# የዘር ልዩነት

ኢጣሊያ አዲስ አበባ ገብቶ ኢትዮጵያን ያዝኩ ብሎ ካወጀ በኋላ አዲስ አበባ ከተማ በተያዘ በ15 ቀኑ እ.ኤ.አ. ግንቦት 21 ቀን 1936 ዓም በወጣው ጋዜታ ዴል ፖፖሎ በሚባለው ጋዜጣ ላይ የፋሽስት መንግሥት የክልሶች መንግሥት መሆን የለበትም በሚል ርዕስ አንድ ጽሁፍ አወጣ ። ጋዜጣው ይህን ጽሁፍ ያወጣበት ምክንያት በኤርትራ ክፍለ ሀገር ውስጥ ብዙ ክልሶች ተወልደው ስለነበር ያን ጠቃቅሶ መላው ኢትዮጵያም እንደ ኤርትራ እንዳይሆን ይታሰብበት ማለቱ ነው ።

ጋዜጣው ይህን በጻፈ በሁለተኛው ቀን ኒውስ ክሮኒክል በተባለው ጋዜጣ ላይ «.....በሮም ውስጥ የተሰበሰበው የሮም ሚኒስቴር ትናንት አንድ ውሳኔ አሳለፈ ። ውሳኔውም በአቢሲኒያና በሌላውም ቀኝ ግዛት ያሉ ያገር ተወላጆች ሁሉ ተለይተው መኖር አለባቸው ። ከዚህም ሌላ በተለይ ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩ ኢጣሊያኖች ሁሉ ሚስት ያላቸው መሆን አለባቸው ። ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡም ከሚስታቸው ጋር እየሆኑ ገብተው አዲሱን መንግሥት እንዲገነቡ ያስፈልጋል ።

«.....በዚህ አዋጅ መሠረትም በሮማ ሱቆችና በዕቃ መደርደሪያ መስኮት ውስጥ እየተቀመጡ ለሕዝብ እንዲታዩ የተደረጉት የኢትዮጵያ ሴቶች ፎቶግራፍ በሙሉ መጥፋት አለበት...የጦር ዜማ ነው የተባለው ፋቼታ ኔራ (ትንሿ ጥቁር ፊት) የሚባለው ዜማና ግጥም እንዳይዘምም ፥ እንዳይገጠምም ተከልክሏል...» የሚል ዜና አወጣ ።

አብዛኛዎቹ የኢጣሊያ ጋዜጦች ፋቼታ ኔራ የተባለው ዜማ እንዲጠፋ ቢከራከሩም ሕዝቡ ግን እያዜመ አስቸገረ ። በተለይ የኢጣሊያ ወጣቱ ክፍል ቀን ቀን የፋሺስት ዜማ ሲያዜም እየዋለ ማታ ማታ ፋቼታ ኔራን ይዘምር ጀመር ።

ፋቼታ ኔራ የፍቅር ዜማና ግጥም ነው ። የኢጣሊያ ወታደር ለጦርነት ተሰልፎ በነበረ ጊዜ ፋቼታ ኔራ መዝሙር በመውጣቱ የኢጣሊያ ወታደር በሙሉ ፋቼታ ኔራን እያዜመ ወደፊት ይገፋ ነበር ። የዚያን ጊዜ ክልከላው ባይጠነክርም ኢጣሊያውያን ከኢትዮጵያውያን ጋር በፍቅር ከተሳሰሩ ለፋሽስት ዓላማ አደገኛነቱ ስለታወቀ ዜማው እንዳይዜም አዲስ አበባ በተያዘች በ15 ቀን በአዋጅ ተከለከለ ።

ፋቼታ ኔራ ትንሿ ጥቁር ፊት

ኮረብታ ላይ ሆነሽ ባህሩን ታያለሽ
ጠይሟ ውብ ቆንጆ የባርያ ባርያ ተብለሽ ።
እንደ ሕልም ሆኖ ላንቺ ይታይሻል
ብዙ መርከቦች ሰንደቁን ቀለማት ያውለበልቡልሻል ።

አንቺ ጥቁር ፊት
ያበሻ ውቢት
ጠብቂ በጉጉት
ደርሷል ያ ሰዓት ።
ስንቀርብ ስንጠጋሽ
አለ የምንሰጥሽ ።

ዱቼና ቄሣርን
እንሰጥሻለን ።

አንቺ ጥቁር ፊት
የአበሻ ወጣት ።
እንወስድሻለን
ወደ ነፃዋ ሮማችን ።
በኛ ፀሐይ ትሳሚያለሽ
ጥቁር ሸሚዝም ትለብሻለሽ ።

አንቺ ጥቁር ፊት
የአበሻ ወጣት
ጠብቂ በጉጉት
ደርሷል ያ ሰዓት ።
ስንቀርብ ስንጠጋሽ
አለ የምንሰጥሽ ።
ዱቼና ቄሣርን
እንሰጥሻለን ።

ወደ አማርኛ ሲተረጐም ይሄ ነው የፋቼታ ኔራ ግጥም ። አዲስ አበባ እንደ ተያዘች ይሄ ዜማ በአዋጅ በመከልከሉ የፋሺስት ዓላማ ምን መሆኑ በመላው ዓለም ታወቀ ። የነፃዎቹ አገሮች ነፃ ጋዜጦችም የኢጣሊያን መንግሥትና ጋዜጦችን እያ ወገዙ ይጽፉ ጀመር ። ግን ጩኸታቸው ተቀባይ ስለሌለው ጥር 2 ቀን 1929 ዓ.ም ሲኞር ሙሶሊኒ "…..በአበሻ ምድር ማንም ነጭ ከማንም ጥቁር ጋር እንዳይገናኝ" የሚል አዋጅ አወጣ ። በአዋጁም ውስጥ '…አጣሩ ። በትክክልም ሁለቱን ትው ዶች (ጥቁርና ነጭን) ለዩ….." የሚል ቃል ነበረበት ።

ስለ ቅኝ ግዛቶች የሚነጋገረው 3ኛው ጉባዔ እ.ኤ.አ. በሚያዝያ ወር 1937 ዓ.ም. ኢስቲቱዮ ኮሎኒያሌ ፋሺስታ የሚባለው ፍሎሬንስ ከተማ ውስጥ ተሰብስቦ ሲነጋገር ብዙውን ጊዜ የያዘው የጥቁርና የነጭ ጉዳይ ነበር ። ከተናጋሪዎቹ አንዱ የሮም ዩኒቨርስቲ መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር ጄናሮ (Gennaro) ሲናገሩ "…..በኢጣሊያኖችና በአገር ተወላጆች (ጥቁሮች) መሀል ያለውን ልዩነት ለመቆጣጠር ገዢና ተገዢው ፣ የሰለጠኑና ኋላ ቀር የወጣው አውሬ ሕዝብ በሥራም በሌላም እንዳይገናኙ ማድረግ ነው…." አሉ ። ሌላው ተናጋሪ ፕሮፌሰር ሬንዞ ሳሊስ (Renzo Salis) ደግሞ ፕሮብሌሚ ኢንዲጂኒ ሱል ፒያኖ ዴል ኢምፔሮ በሚል ርእስ ጀምረው ሲናገሩ "……..ወደድንም ጠላን እነኚህ ጥቁሮች በግዛታችን ውስጥ ናቸው ። ግን የኛ ዘሮች አይደሉም ። መንግሥታችን ይግዛቸው እንጂ ከኢጣሊያ ሕዝብ ወይም ከነገዱ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም ። ግንኙነታቸው በተገዢነት ብቻ ነው ።…… ነፃነት ፣ እኩልነት ፣ ወንድማማችነት የሚለው የላቲን ተረት መለወጥ አለበት ። ለውጡም ትእዛዝ ፣ ሥልጣን ፣ ፍርድ መሆን አለበት ።…" አሉ ።

ጆርጆ ሳን ጆርጂ (Giorgio San Giorgi) በዚያው ስብሰባ ላይ ኡን ፕሮብሌማ ዲ ኢቪታሬ ኤል ሚቲካቶ በሚል ርእስ ተነስተው ሲናገሩ "……የእ ባት አገራችንን ክብር እንጠብቃለን ።….. ዱቼ የመሠረቷት የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛታችን በብዙ ሚሊዮን በሚቆጠሩ ኢጣሊያውያን ትሞላለች ።……ያን ጊዜም ንፁሑ ደማችን ንፁህ እንዲሆን ይኖራል ። ለዚህም ያለን አመራር ክብረት የጠነከረ መሆን አለበት ።……" አሉ ። ፕሮፌሰር ማሪኖ ሙቲኔሊ (Marino Mutinelli) ደግሞ "…በቅኝ ቅዛት ውስጥ ከባድ ችግር የፈጠሩት እነኚህ ከኛ ደም የተቀላቀሉት ክልሶች ናቸው ። በተፈጥሮአቸው ደካሞች ፣ ረፍት የሌላቸው ቀዥቃዦች ናቸው ።

ብዙውን ጊዜም ለቅኝ ግዛቶች ለወጣው ሕግ አይታዘዙም ፡፡ ስለዚህ እነሱን አስ ቀድሞ መለየት ያስፈልጋል ፡፡...” ብለው ተናገሩ ፡፡

የሴቶች ተወካይ ሆነው በጉባኤው የነበሩት ፕሮፌሰሯ አና ጋሊ (Anna Galli) በተራቸው ሲናገሩ “.........ዋናው ነገር በቅኝ ግዛቶቻችን ያሉ ኢጣሊያ ሴቶች ሁሉ ክብራቸውን መጠበቅ አለባቸው ፡፡ ከወንዶቹ የበለጠ ጥንቁቆች ሆነው የገዢነት ክብራቸውን ማሳየት አለባቸው ፡፡....ኢጣሊያ ኢጣሊያ ነች ፡፡ ኢጣሊያ በማይረባ ደም እየተደባለቀች ክብርዋ ሊጐድፍ አይገባም ፡፡ ሮማና ታሪኳ እንደተከበሩ ይቆያሉ ፡፡ .....” ሲሉ ተናገሩ ፡፡

ይህ በፍሎሬንስ ከተማ የተካሄደው ጉባኤ ሲፈፀም በኢጣሊያ ንጉሥ በቪቶሪዮ አማኑኤል ሳልሳዊ ፊርማ የፀደቀ አዋጅ እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 19 ቀን 1937 ዓ.ም (በኛ አቆጣጠር ሚያዝያ 11 ቀን 1929) ወጣ ፡፡ ከአዋጁም ጥቂቱ እንዲህ የሚል ነው ፡፡ “ማንኛውም ኢጣሊያዊ ዜጋ በኢጣሊያ ምድር ሆነ በቅኝ ግዛት አገሮች ያለ ኢጣሊያዊ ሁሉ ፣ በተለይ በምሥራቅ አፍሪካ ካሉ ጥቁሮች ወይም በባህሉ ከማይስማሙ ነጮችም ጋር ግንኙነት ሲያደርግ የተገኘ እንደሆነ ከአንድ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል ፡፡.....”

እ.ኤ.አ. ሴቴምበር 18 ቀን 1938 ዓ.ም. (በኛ አቆጣጠር መስከረም 8 ቀን 1931 ዓ.ም ) ሙሶሊኒ አንድ ዲስኩር ተናገረ ፡፡ “...ይሄ የዘር መለየቱ ጉዳይ እንደ ተጠበቀው አልሆነም ፡፡ አሁንም የሰደደውን ሥር አልነቀለም ፡፡ ታሪክ እንደሚያስተምረን ኃይለኛ መንግሥት በወታደሩ ኃይል ሌሎች አገሮችን ያስገብራል ፡፡ ግን ክብሩን ሳይጥል ክብሩን ጠብቆ መሆኑ ይታወቅ....” አለ ፡፡ ይህ የሙሶሊኒ ዲስኩር በቅኝ ግዛቶች ሁሉ ከተሳለፈ በኋላ ሙሶሊኒ ዲስኩር ባደረገ በ3ኛው ቀን ማለት ሴቴምበር 21 ቀን (በኛ መስከረም 11 ቀን) አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አንድ አዋጅ ወጣ ፡፡ አዋጁም እንዲህ ይላል ፡፡ “....ለሕዝባችን ጤንነት ፣ ለኢጣሊያኖች ክብር ስንል ቀጥሎ ያለው ታውጅዋል ፡፡ ማንኛውም ኢጣሊያዊ ቀርቶ ፣ ከውጭ የገባ የውጭ አገር ሰውም ቢሆን ለጥቁሮች ከተከለለው ከተማ እንዳይደርስ ፣....ማንኛውም ኢጣሊያዊ ሆነ ወይም ከውጭ የገባ የውጭ አገር ሰው ፣ ከማንኛውም ጥቁር ወይም የአገር ተወላጅ ጋር ንክኪ እንዳያደርግ ፣.... ለጥቁሮች ከተከለለው ክልል ወደ ተክለሃይማኖት አካባቢ ወይም ከአዲሱ ከተማ ፣ ጉዳይ ወይም ሥራ ኖሮት ለመግባት የሚፈልግ ማንኛውም ኢጣሊያዊ ወይም ከውጭ የገባ የውጭ አገር ተወላጅ ከመግባቱ በፊት ከባለ ሥልጣኖች ፈቃድ እንዲቀበል ፣...ማንም ኢጣሊያዊ ወይም ከውጭ የገባ የውጭ አገር ሰው ለጥቁሮች ከተከለለው ከተማ የፖሊስ የይለፍ ፈቃድ ሳይኖረው እንዳይገባ ተከልክሏል .....” የሚለው አዋጅ ኮሪየሬ ዴል ኢምፔሮ በተባለው አዲስ አበባ ውስጥ እየታተመ በሚወጣው ጋዜጣ ላይ ታትሞ ወጣ ፡፡ በዚያው ዘመን ሴቴምበር 26 ቀን (በኛ መስከረም 16 ቀን) የወጣው ለንደን ታይምስ ጋዜጣ ደግሞ ጥቁሮች በሚነዱት መኪና ነጮች እንዳይቀመጡ መከልከሉን አወራ ፡፡

የጀርመን ናዚ ያወጣውን አመራር የኢጣሊያ ፋሺስት መንግሥትም በመከተል የዘር ልዩነት መመሪያ የሆነውን ላ ዱፌሳ ዴላ ራዛ የተባለው የአመራር መምሪያ (የፖሊሲ) መጽሐፍ እ.ኤ.አ. ነሐሴ 5 ቀን 1938 ዓም ታትሞ በሥራ ላይ እንዲውል ተደረገ ፡፡ የመጽሐፉ መሸፈኛም የሮማዊው ሐውልት በብረት ሰይፍ ከአይሁዶችና ከጥቁሮች ሲለይ የሚያሳይ ነበር ፡፡

ጁሴፔ ፋብሪ የተባለ የፋሺስት ፓርቲ አባል “ኢትዮፒያ” በተባለው ሮማ በሚታተመው ጋዜጣ ላይ Razza E Dominio በሚል ርእስ ተነስቶ “......በቅኝ ግዛት ያሉት መኰንኖቻችን ከጥቁር መኳንንቶችና ሠራተኞች ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነት በጥብቅ እንቃወማለን ፡፡ እነኚህ ጥቁሮች ከኛ ሰዎች ጋር የሥራ ግን

ኙነት በሚያደርጉበት ጊዜ ሕሊና የሌላቸው ፍጡሮች በመሆናቸው ከኛ ሰው ጋር እኩል የሆኑ ይመስላቸዋል ። እንዲህ ዓይነቱ ግንኙነት ከቀጠለም አገራችን በበ ሽታ (በጀርም) መበከሏ ነው ።....የጥቁሮቹ ቢሮ ከነጮቹ ቢሮ በጣም በሩቀ ቦታ መሆን አለበት ። ጥቁሮቹ ለነጮች ፋይሎችን በሚያቀርቡበት ጊዜ እጃቸው ፋይ ሉን እንዳይነካው ፋይሉን በሌላ በንፁህ ወረቀት መያዝ አለባቸው ። ....ታላቁ የተከበረ ደም ያለበት ታላቁ ኢጣሊያዊ በማያውቀው አገር ገብቶ የቋንቋ ችግር ስለሚያጋጥመው አስተርጓሚ ያስፈልገዋል ይባላል ። ስህተት ነው ። አስተርጓሚው በሽታ እንዳያጋባበት ኢጣሊያኖቹ በአስቸኳይ ቋንቋ የሚማሩበት ዘዴ መፈጠር አለበት ። ....እንዲህ አድርጎ ታላቁ የፋሺስት መንግሥት የታላቂቱን ኢጣሊያ ዜጋ ክብር መጠበቅ ይገባዋል....” ሲል ፃፈ ። በዚህ ጽሑፍ መሠረትም ኢጣሊ ያውያን ፣ አማርኛና ኦሮምኛ ቋንቋ የሚማሩባቸው ሁለት መጽሐፍት ታትመው ወጡ ። እነዚህ መጽሐፍትም ከኔ ዘንድ ይገኛሉ ።

እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 19 ቀን 1937 ዓ.ም. (በኛ አቆጣጠር ሚያዝያ 11 ቀን 19 29 ዓ.ም. ) አንድ ተጨማሪ አዋጅ አዲስ አበባ ላይ ወጣ ። ከአዋጁ ልጦቃቅስና አንቀጽ 11 ላይ “....ይህ አዋጅ ከታወጀበት ከሚያዝያ 19 ቀን በኋላ ማንኛውም ኢጣሊያዊ ዜጋ ከጥቁር ሴት ልጅ ቢያስወልድና ልጁን አምኖ ቢቀበል በዚህ በወ ጣው ሕግ መሠረት ይቀጣል ።....” ይልና በአንቀጽ 12 ላይ ደግሞ “.....ማንኛ ውም የኢጣሊያ ዜጋ ለጥቁሮች ከተከለለው ሥፍራ ያለፈቃድ ገብቶ ቢገኝ እስከ ስድስት ወር በሚደርስ እሥራት ወይም እስከ ሁለት ሺ ሊሬ በሚደርስ ቅጣት ይቀጣል.....” ይላል ።

13ኛው አንቀጽ ላይ ደግሞ “......አንድ ጥቁር የሚያሠራውን ሥራ አንድ ኢጣሊያዊ ፣ ያለ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ሥራውን ለመሥራት ቢስማማ 500 ሊሬ ይቀ ጣል ።......” ይልና አንቀጽ 14 ላይ ደግሞ “.......አንድ ኢጣሊያዊ ወይም የኢ ጣሊያ ዜጋ ለጥቁሮች ከተከለለው ሠፈር ካሉት መጠጥ ቤቶች ገብቶ ሲጠጣ ቢገኝ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም ከሁለት መቶ እስከ 500 ሊሬ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ።.....”ይላል ። 17ኛውና 18ኛው አንቀጽ ደግሞ “.....ማንኛውም የአገር ተወላጅ ጥቁር ፣ ከኢጣሊያ ዜጎች ጋር ግንኙነት ቢያደርግ እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ እሥራትና እስከ አሥር ሺ ሊሬ ድረስ ይቀጣል.....” ይላል ።


ይህ ሁሉ አዋጅ ቢታወጅም የፋሺስት ባለሥልጣኖች ለፕሮፓጋንዳ እየተባለ በፈቃድ ከጥቁሮች ጋር ቢገናኙም ፣ ተራው ወታደርና ሲቢሉ ተራ ኢጣሊያዊ ግን አዋጁን ተቀብሎ በተግባር አላዋለውም ነበር ። ስለዚሁ ጉዳይ ማስረጃ እንዲሆን በዘመኑ የታወቁ ኢጣሊያዊ ፀሐፊ ዳንቴ ጋሊአዚ (Dante Galeazi) እ.ኤ.አ. በ1959 ዓ.ም. ባሳተመውና ኢል ቪዮሊኖ ዲ አዲስ አበባ በተባለው መጽሐፉ ውስጥ ያሰፈረውን ታሪክ ለማቅረብ ፈለግሁ ። እንዲህ ይላል ።“......አበሻ ሴት ጐጆ ውስጥ ሁለት የኢጣሊያ ወታደሮችን አገኘሁ ። አንደኛው የብርጌድ ጦር አዛዥ ነው ። ሙሶሊኒ ስላወጣው ክብረት የጠነከረ ደንብ ጉዳይ አነሳሁና ለምን ከጥቁር ሴት ቤት እንደገቡ ጠየቅኋቸው ።.....ልክ ነህ ፣ ሕግ ሕግ ነው ። ነገር ግን ካራቢ ኔዮሮቹም (ፖሊሶቹ) እንደኛው ሰው ናቸው ። በእንዲህ ዓይነቱ ቦታ ሲያዩንም አይና ቸውን ጨፍነው ያልፋሉ ። ምክንያቱም እነሱም እንደኛው ናቸው ። የእንቁላል ችግር አለብን ። ብዙ ጊዜም እንቁላል ለመግዛት ከካምፕ እንወጣለን ። ከእንዲህ ዓይነቱ እንቁላል ካለበት ቤትም በተራ እንገባለን። አሁንም ከእነኚህ ጥቁር ሴቶች ቤት የገባነው እንቁላል ልንገዛ ነው.... አሉኝ ። እኔም ቶሎ ብዬ ከዚያ ቤት ወጣሁና ራቅ ብዬ ተደብቄ ቆሜ እጠባበቃቸው ጀመር ። እኩል ሰዓት ያህል እንደቆዩ ሁለቱ ወታደሮች እየተሳሳቁ ከቤቱ ወጥተው ጉዞአቸውን ጀመሩ ። እንቁላሉን ግን አል ያዙም ነበር ። .....”

እ.ኤ.አ. በታህሳስ ወር 1940 ዓም ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው ቶርዲኒ የተባለ አይሮፕላን ነጂ ሲገልጽ«.....ሕጉን ማክበር እንዴት ይቻላል? ክብራችንን ለመጠበቅ ከጥቁሮች ጋር እንዳንገናኝ ተወስኗል ። በአንድ አካባቢ እንኖራለን ። ከባድ የቤት ችግር ስላለም ባንድ ግቢ ውስጥ ተደባልቀን እንኖራለን ። ባንድ መንገድ ላይ እንሄዳለን ....። ብዙ ነጭ ሠራተኞች ከጥቁር ሠራተኞች ጋር ጐን ለጐን ሆነው አንድ ዓይነት ሥራ ይሠራሉ ። ብዙ ነጮች ልክ እንደጥቁሮች ሸክም እየተሸከሙ ይሠራሉ ። ...በብዙ ቦታም አብረው ሲሰሩ የዋሉ ነጮችና ጥቁሮች ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፈው ወደመደሰቻ ቦታ ይሄዳሉ ። እንዲህ ዓይነቱን ግን ያኔ መናገሩ ማስጨረስ ነበር ።...» ማለቱን ዶወር ባሳተመው አቢሲኒያን ፖችወርክ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ገልጾታል ።

———o———

# ዘርአይ ድረስ

አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የምድር ባቡር መድረሻና መነሻ የሆነው ጣቢያ ከተሠራ በኋላ በሕንፃው ፊት ለፊት ካለው ሜዳ ላይ የአንበሳ ሐውልት ተሠርቶ ቆመ ። ኢጣሊያኖች አዲስ አበባን እንደያዙ ያን ያንበሳ ሐውልት ከቆመበት አውርደው ወደ ሮማ ወሰዱት ።



ዘርአይ ድረስ ።

በ1929 ዓም ኢጣሊያ አዲስ አበባ የገባችበትን አንደኛ ዓመት ለማክበር ሮማ ውስጥ ታላቅ በዓል ተደርጐ ነበር ። በዚያም በዓል ላይ የኢጣሊያኑ ንጉሥና ሙሶሊኒ ተገኝተው ነበር ። ከኢትዮጵያ ተማርኮ የተወሰደው የአንበሳው ምስል በዓሉ በሚከበርበት አደባባይ መሐል ቆሞ ለሕዝብ ይታያል ።

ዘርአይ ድረስ የተባለ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ተወላጅ በበዓሉ አከባበር ሥነ ሥርዓት ይላ ለኢጣሊያኑ ንጉሥና ለሙሶሊኒ ሥጦታ የሚሆን ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ዕቃዎችንና ጐራዴ ጭምር ይዞ ሄዷል ። ዘርአይ ድረስ የዚያን ጊዜ ዕድሜው 21 ዓመት ነው ። ዘርአይ በኢጣሊያኖች መራጭነትና ትእዛዝ ለኢጣሊያ ንጉሥና ለሙሶሊኒ የሚሰጠውን የጥቁሮችን ገፀ በረከት በጥቁር እጁ ይዞ ንጉሡና ሙሶሊኒ ወዳሉበት ሠገነት ሲያመራ የተማረከው ሀውልታችን ከአደባባዩ መሐል ቆሞ ኢጣሊያኖች ሲፎክሩበትና ሲጨፍሩበት አየ ።

በሥፍራው የነበሩ ያይን ተመልካቾች እንደፃፉት «.....ዘርአይ ዓይኑ ደፈረሰ ። ካለበት ቦታ ተንበርክኮ ፀለየ ። ከፀለየ በኋላ ለሥጦታ የያዘውን ጐራዴ መዝዞ ወደ አንበሳው ገሠገሠ ። የዘርአይን ሩጫ ያዩ ሁለት ፖሊሶች ሊያቆሙት ያዙት። በጐራዴው መቷቸው ። እንደ እብድ የሆነው ዘርዓይ ድረስ አከታትሎ አምስት የፋሽስት መኰንኖች ገደለ ። ከዚህ በኋላ በጥይት ተመትቶ ወደቀ ።

«የዘርአይ ድረስ ቁስል ከባድ ስለነበረ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ ። ከዳነም በኋላ ባንዲት ደሴት እሥረኛ ሆኖ ጥቂት ዓመታት እንደቆየ ሞተ...» በማለት ጉል ደን ሳይን በሚባለው መጽሐፉ ሐርትሜየር ጽፏል ። የማይደንቀው ታላቅ ጀግና ነው ።

—O—



ዘርአይ ድረስ።

## ፲፱፻፴

«ማርሻል ግራዚያኒ ፡፡ የሚደርሰንን ሪፖርት ሁሉ አንብበን አጥንተነዋል ፡፡ ሽፍቶቹ በየቦታው እየተዘዋወሩ ጥቃት ማድረሳቸውን በሚገባ አጥንተነዋል ፡፡ ይህም በመላው ዓለም የፋሽስትን መንግሥት የፖለቲካ አመራርና የወታደራችንን ጥን ካሬ የሚያስድብ ይሆናል ፡፡ ባለፉት ሣምንታት የተላለፉትን ሪፖርቶች እንዳየኋ ቸው የሽፍቶቹ ማጥቃት የሚያሳፍረን ነው ፡፡ አሁንም ያስፈለገው ወጭ ወጥቶ ፣ የሚ ከፈለው መስዋእትነት ተከፍሎ በአጭር ጊዜ እንዲደመሰሱ ያስፈልጋል ሲሉ ዱቼ ሙሶሊኒ እዘዋል ፡፡

ሌሶና»

የቅኝ ግዛት አገሮች ሚኒስትር በክረምቱ ወራት የደረሰው የኢጣሊያ ሠራ ዊት እልቂት አሳፋሪ መሆኑን የገለጡበት ቴሌግራም ነበር ፡፡ ሚኒስትሩ ይህን ቴሌግራም በላኩ በማግሥቱ ማለት መስከረም 2 ቀን ደግሞ «..... እንዳጠናሁት የኢጣሊያ ሠራዊት መግፋት ያቃተው ሽፍቶቹ በሚያደርሱት መሰናከል ነው ፡፡ ስለዚህ ወታደራችን ከመዝመቱ በፊት ሽፍታ ያለበት ቀበሌ በሙሉ መርዝ ጋዝ ይረጭበት ፡፡ ከዚያ በኋላ ወታደሮቻችን በባዶ ሜዳ መንዝ ይችላሉ ፡፡ ይጠቀሙ በት....» የሚል ቴሌግራም አከታትለው ለግራዚያኒ ላኩ ፡፡ ይህ ቴሌግራም ለግራ ዚያኒ ከተላከ ከሶስት ቀን በኋላ ዱቼ ሙሶሊኒ ደግሞ «....ብዙ ባታሊዮን ጦርና ብዙ አይሮፕላኖችን ለመላክ ተዘጋጅቼአለሁ ፡፡ ባለን ኃይል ሁሉ ተቃዋሚዎቻችንን ማጥፋት አለብን ፡፡ የሚጠፉትም ደግሞ በአጭር ጊዜ መሆን አለበት ፡፡ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ ጊዜ እንዳታጠፉ፡፡.....» የሚል ትእዛዝ ለግራዚያኒ አሳለፉ ፡፡

በዚህ ዘመን በኢጣሊያ ሠራዊት ላይ ከባድ ፈተና ወድቆ ነበር ፡፡ ግራዚያኒ በጦር ኃይል ያልቻለውን በእርቅ ለመጨረስ ወደራስ አበበ አረጋይ መልእክተኛ መላክ የጀመረው በዚህ ዘመን ነው ፡፡ ቺያኖ በያዘው ማስታወሻ «.....መስከረም 3 ቀን ጐጃሞች ባደረሱት እልቂት ሙሶሊኒ በጣም ተናደዱ.... መስከረም 7 ቀን በደረሳቸው ሪፖርት መሠረት በጣም ተበሳጭተው የሚናገሩትንም አያውቁም ነበር ፡፡ በመጨረሻም ብቻ በጋዝ ፣ በጋዝ ፣ አዎን በጋዝ መጨረስ አለብን ፡፡ በአስ ቸኳይ ትእዛዝ ይተላለፍ፡፡...አሉ ...» ይላል ፡፡

በመስከረም ወር ባላመነው ክፍል ላይ የመርዝ ጋዝ ሲረጭበት ከረመ ፡፡ በተ ለይ ጐጃምና ጐንደር በሚገባ ተረጨባቸው ፡፡ ሙሶሊኒ መስከረም 21 ቀን ለግራ ዚያኒ በላኩት ቴሌግራምም «.....አዲስ ያልተነካ አራት ክፍለ ጦሮች ልኬልሃለሁ ፡፡ በተቻለ መጠን በአስቸኳይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተቃዋሚዎቻችን እንዲጠፉ ይሁን ፡፡ .....» አሉ ፡፡ ሌሶና ደግሞ መስከረም 28 ቀን በላኩት ቴሌግራም «.....እደግመዋ ለሁ ፡፡ ክቡርነትዎ የሚያስፈልግዎን ያህል ወታደር እልክሎታለሁ ፡፡ እደግመዋለሁ ፣ ሽፍቶቹ በአስቸኳይ መጥፋት አለባቸው ፡፡.....» አሉት ፡፡ ግራ የገባው ግራዚያኒ የሌ ሶና ቴሌግራም በደረሰው ማግስት በቴሌግራም«.....ታክቲክና የጦር ዘዴ ያስፈ ልገዋል ፡፡.....በተግባር የተገኘው ትምህርት እንዳስተማረን ሽፍቶቹን በውጊያ መጋ ጠም ይቻላል ፡፡ ማጥፋት ግን አይቻልም ፡፡.....» የሚል መልስ ሰጠ ፡፡

ጠቅላይ የኢትዮጵያ ገዥ የነበረው ማርሻል ግራዚያኒ ጥቅምት 25 ቀን ወደ ሮማ ባስተላለፈው መልእክት«.....አሁን ያሉት የኢጣሊያ ወታደሮች 111.500 ናቸው ፡፡ .....ዋናው የሚያስፈልገው ነገር ፣ 1/ የዋናው ከተማ ፀጥታ የተጠበቀና እሸ

ተማማኝ እንዲሆን በወታደርና በሌላም መታጠር አለበት ። 2/ በባቡሩ ሐዲድ ላይ ተንቀሳቃሽ የሆነ እየተመላለሰ ፀጥታውን የሚጠብቅ የተጠናከረ ኃይል ያስፈልጋል ። 3/ የሸዋ ሕዝብ ታማኝ መስሎ በሽፍታዎች የተጠናከረ ስለሆነ ደብረ ብርሃንና ፍቼ ከተማ ጠቅላይ ቢሮው ሆኖ ጠንካራ ተዘዋዋሪ አዳኝ ቡድን ተቋቁሞ ወደዋናው ከተማ የሚመጡትን ሽፍቶች እንዲቆጣጠር ፤ 4/ እንደዚሁ ተመሳሳይ የሆነ የጦር ክፍል በምዕራብም ተቋቁሞ የመገናኛ መስመሮችን እንዲጠብቅና እንዲቆጣጠር ያስፈልጋል ።.....»የሚል አሳቡን ላከ ። መልስ ግን ፈጥኖ አላገኘም።

እ.ኤ.አ. ኅዳር 26 ቀን የወጣው ዘ. ታይምስ ጋዜጣ «..... እስከ መጭው ክረምት ድረስ የአገሪቱን ፀጥታ ለማስከበር ታስቧል ። አሁን ግን ሁኔታው ጥሩ አይደለም ። ከአዲስ አበባ ጂማና ጐሬ የሚወስደው መንገድ ከአዲስ አበባ 50 ማይልስ ርቀት ላይ ተሰብሯል ።......በየትም አቅጣጫ ቢሆን ትራንስፖርት መኪናዎች የሚጓዙት በሕብረትና በወታደር እየታጀቡ ነው ።.....»የሚል ዜና አወጣ ። በዚህ በጋዜጣው ዜና ሙሶሊኒ ተበሳጩ ። ግራዚያኒንም በተለመደ ቁጣቸው ተቆጡት። ግራዚያኒም ለጂማና ለሐረርጌ ገዥዎች ጥቅምት 30 ቀን ባስተላለፈው ትእዛዝ «...ለዚህ አገር ሕዝብ ፖለቲካ አያስፈልገውም ። ማባበልም አይገባም ። ሰው ሲበሳጭ ይሸፍታል የሚባለውንም አላምንበትም ።.....የመጨረሻ ትእዛዝ የምነግራችሁ ትንሽ ትልቅ ሳትሉ....እንድትፈጁት ።.....ርህራሄ ማድረግና ማዘን አያስፈልግም ።.....ይሄ የኔ መመሪያ ነውና የአማራን ጐሣ በሙሉ ጨርሱ ። አዝዣለሁም ።....» ካለ በኋላ በዚያው ዕለት ወደሮማ ባስተላለፈው ቴሌግራም «....ካላለቁ ሰላም እንደማይገኝ አውቃለሁ ። ጨርሷቸው ፤ ፍጅዋቸው ። ጨርሷቸው ፤ ፍጅዋቸው ። ጨርሷቸው ፍጅዋቸው እያልኩ ደጋግሜ ትእዛዝ አስተላልፌአለሁ ። አስቸጋሪ ሕዝቦች ናቸው ።ባለቁና ከቢሮዬ ቁጭ ባልኩ ።.....» በማለት የመረረ ሪፖርት አቀረበ ። በግራዚያኒ የድፍረትና የመስልቸት አመላለስ ዱቼ ሙሶሊኒ ተናደደ ። ታህሳስ 17 ቀንም ግራዚያኒን አንስተው በሱ ቦታ የአኦስታውን መስፍን (ዱካ.ዲ. አኦስታ) ሾሙ ።

የአኦስታው መስፍን ከእንግዲህ ወዲያ ዱካ ዲ. አኦስታ እያልኩ የምጠራቸው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አብሮአቸው የመጣ ኡጐ ካቫሌሮ (Ugo Cavallero) የሚባል ቺፍ ኦፍ እስታፍ ነበራቸው ። ይህ ሰው ስለዚያን ጊዜው ሁኔታ ሲጽፍ «....አሮጌ ዎቹ ቅኝ ግዛቶቻችን ኤርትራና ሶማሌ በሚገባ የተደራጁ ናቸው ። .....አብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ግን ሸፍቷል ። የደቡባዊው ኤርትራም የጠራ አይደለም ።ትግሬ ው ስጥም ደህና ነው የሚባለው በመጠኑ ነው ። ብረት የያዙ ባላገሮች ገና በመዘዋወር ላይ ናቸው ። እነዚህ መሣሪያ ያላቸው ባላገሮችም የሚታዘዙት ለራሳቸው አለቃ ብቻ ነው።.....ወደኛ ግን እነጣጣሪው ብዙ ነው ።.....እምኒል የሚባለው ሕዝብም ሽፍታዎቹን ሙሉ በሙሉ ይረዳቸዋል ።.....እያንዳንዱ የሽፍታ ቡድን ብዙ ሰዎች ያሉበት ነው ። ከሰዎቹም መሀል ጠመንጃ የሌላቸው ጦርና ዱላ ብቻ ይዘው የሚከተሉ አሉ ። እነኚህም ጠመንጃ የሌላቸው ሽፍቶች ከኛ ሠራዊት ጋር ግጥሚያ በሚደረግበት ጊዜ ከዚያ እናገኛለን እያሉ በተስፋ የሚከተሉ ናቸው ። በዚህም ምክንያት ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ ያለምንም ፍርሐት ከመሀል እየገቡ የሚያተራምሱ እነሱ ናቸው ።.....በየትም ቦታ ሽፍታው ስለአስቸገረ ኢንዱስትሪዎች ባሉበት ባንዳንድ አስፈላጊ ቦታዎችና በመንገዶች ላይ ለወታደሮች መጠበቂያ የሚሆኑ ቤቶች መሥራት ጀመርን ። ምክንያቱም በሽፍቶቹ ምክንያት ሥራው ሁሉ ይቋረጥብን ስለነበር ነው ። መንገደኞችም የሚጓዙት በአጀብ ስለሆነ በየመንገዱ የሚሠራው የጥበቃ ቤት መፍትሔ ይሆናል ብለን አስበናል ።...» ይላል ። እነኚህ ለጥበቃ ተብለው የተሠሩት ቤቶች ይህ መጽሐፍ እስከታተመበት ጊዜ ድረስ በየዱሩ ፍርስራሻቸው ይታያል ። በዚያን ጊዜ 300 የፍተሻ ጣቢያዎች (Posti di Bloco) በየመንገዱ ላይ ሲሰሩ ለፖሊስ የጥበቃ ቦታዎች ደግሞ በየኮረብታው ላይ 13,000 ምሽጐች መሠራታቸውን ኢል ላ እኖ ዴል ኢምፔሮ የተባለው መጽሐፍ ገልጦታል ።

እንደገና የሙሶሊኒ ቁጣ ያየለው በታህሣስ ወር ነው ። የሙሶሊኒን ቁጣ ታህ ሣስ 30 ቀን ቼአኖ ወደ ኢትዮጵያ ሲያስተላልፍ “......ዱቼ ሙሶሊኒ በኢትዮጵያ ግዛት ምክንያት እጅግ መናደዳቸውና መቆጣታቸውን እንድገልጽ ታዝዣለሁ ። ጐጃም በሙሉ ሸፍቷል ። በጐጃም ያለው ሽፍታም 15,000 ይሆናል ። ምሽጐቻ ችን እየተጠቁ ናቸው ። ........አሁንም ከባድ ኃይል ተዘጋጅቶ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያመሰሱ አስታውቃለሁ ።” አለ ።

ፌብሩአሪ 4 ቀን የወጣው ኢቭኒንግ እስታንዳርድ የተባለው ጋዜጣ “.....በየም ሽቱ የአበሻ ወታደሮች ኢጣሊያኖች ያሉበትን ቦታ ያጠቃሉ ። ኢጣሊያኖችም እየ ከዳቸው በሚሄደው ወታደር ብዛት እጅ ሰባራ ሆነዋል ።......” የሚለውን እንግሊ ዝኛ ጽሑፍ ሙሶሊኒ ሲያዩ የባስ ተናደዱ ። ወዲያውኑም ኢትዮጵያውያን ለኢጣ ሊያኖች ያስረከቡት የመሣሪያ ብዛት ስንት እንደሆነ በአስቸኳይ እንዲጠየቅ አዘዙ ። በወሬ ሳይሆን በተግባር የሚፈተነው ኢትዮጵያ ያለው የኢጣሊያ ጦር መሪዎችም “......እስካሁን እስከ ጥር ወር ድረስ 297,295 ጠመንጃ ፥ 1542 ሽጉጥ ፥ 1011 ሙትረየስ ገቢ ሆነዋል ።.....” ሲሉ መለሱ ።


ይህ ኢትዮጵያውያን ያስረከቡት የመሣሪያ ብዛት በኢጣሊያ ጋዜጦች ላይ እንደተገለፀ ሎንደን ያለው የዴይሊ ቴሌግራፍ ጋዜጣ ወኪል ለወከለው ጋዜጣ አንድ ሪፖርት ላከ ። “....ይህ ኢትዮጵያውያን አስረከቡ የተባለው የጦር መሣሪያ ፥ ጦር ነቱ ከመነሳቱ በፊት ኢትዮጵያውያን ወዳገራቸው ካስገቡት የጦር መሣሪያ ከሶስት አንዱ እጅ ያህል ነው ። ይሄ ሲታይ እንግዲህ ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያውያኖችን ማስገበር አልቻሉም ማለት ነው ። .....አሁን የሚሻለው ነገር ሮም ፥ ከኤሮፓ ፥ ከግብፅና በሰሜን አፍሪካ ካሉ የፈረንሳይ ግዛት አገሮች ጋር የሰላም ወዳጅነቷን ማጠንከር ነው ። ሮም ይህን ካደረገች ግዛትዋን መግዛትና በእጅዋ ማቆየት ትችላለች። ይህ ሳይሆን ቀርቶ በጦርነት ውስጥ የምትገባ ከሆነ ግን አበሾች ካገራቸው አባር ረው ያስወጧታል ።....” የሚለው ሪፖርት ወጣ ።

ይህን በመሳሰለው ግፊትና በአርበኞች አልበገር ባይነት ዱካ ዲ.አኦስታ አመ ራራቸውን ለወጡ ። ተበታኝ ወረቀቶች እየታተሙ አርበኞች ባሉበት ቦታ ሁሉ በአይሮፕላን ይበተኑ ጀመር ። የሚበተኑትም ወረቀቶች “.......ስሙ ። በሰማይ ሲበር የምታዩት ይህ አይሮፕላን ማንኛውንም ነገር ካስፈለገ ማጥፋት እና መደ ምሰስ የሚችል ነው ። በመሬት ላይ ሲጓዙ የምታዩዋቸው ወታደሮቻችን የሚጓዙት ሥራውን ሁሉ ለማስተካከልና ሰላምን ለመፍጠር ነው ። ስለዚህ የጦር መሣሪያዎ ቻችሁን በየአቅራቢያችሁ ላሉ የጦር አለቆቻችን አስረክቡ ። ይህን ለሚያደርጉ ሁሉ ሙሉ ምሕረት ተደርጓል ። ይህን ባታደርጉ ግን ከሰማይ አደገኛና አስከፊ ዝናብ አዘንብባችኋለሁ ። ሀብታችሁ ፥ ጥሪታችሁ ሁሉ ይጠፋል ። በዚህም ጥፋት ሴቶች ፥ ሕፃናትና በዕድሜ የገፉ ሰዎች አብረው ይጠፋሉ ። ሁላችሁንም አጠፋለሁ” የሚሉ ነበሩ ።

እ.ኤ.አ. ሜይ 14 ቀን 1938 ዓ.ም. የወጣው ኒውታይምስ ኤንድ ኢትዮፒያ ኒውስ የተባለው ጋዜጣ ለንደን ውስጥ የአርበኞችን ዜና ይዞ ወጣ ። “.....ካለፈው የመኸር ወራት ጀምሮ እስካሁን ድረስ በኢጣሊያኖች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል ። ተምቤንና ሰቆጣ በደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ተይዟል ። ሰሜናዊ ምሥራቅ ትግሬን የሚገዙት ደጃዝማች ገብረሕይወት ናቸው እንጂ ኢጣሊያኖች አይደሉም ። በበጌ ምድርም የማያቋርጥ ውጊያ አለ ። ብዙ ጊዜም የኢጣሊያኖች ምሽግ እየተደፈረ ስንቃቸው ሳይቀር ይማረካል ።......በትግሬ ውስጥ የኢጣሊያ ወታደሮች የሚገ ኙት ምሽግ በሠሩባቸው ባንዳንድ ከተሞችና በዋናው ከተማ ብቻ ነው ። ሌላው ከተማና ግዛት ከኢጣሊያኖች ቁጥጥር ውጭ ነው ። በበጌምድር ግዛትም ኢጣሊያኖች ሁለት ቦታ ማለት ደብረ ታቦርና ጐንደር ላይ ብቻ ነው የተጠናከረ ምሽግ ያላቸው ። እነኚህም ምሽጐች ስንቅም ሆነ መሣሪያ የሚደርሳቸው በአይሮፕላን ነው ።

"ጐጃም በሙሉ ለኢጣሊያ አልተገዛም ። ......ከአዲስ አበባ በየቀኑ ሰላሳና አርባ የሚሆኑ አይሮፕላኖች እየተነሱ ሀገሩን በቦምብ ይደበድቡታል ። በግዛቱ ውስጥም ምንም የኢጣሊያ ሠራዊት ስለሌለ ለድብደባው ቦታ አይመርጥለትም ። በወለጋም ኢጣሊያኖች ሁለት ቦታ ላይ ብቻ በተጠናከረ ምሽግ ተቀምጠዋል ።.... ከዚያ አልፈው ተራራዎችንም ሆነ የግብርና ቦታዎችን ለመያዝ አልቻሉም ።ከአዲስ አበባ ጂቡቲ የሚወስደው የባቡር መስመር በየጊዜው ይሰበራል ።...በተጠናከረ ኃይል የሚወጉትን ኢትዮጵያውያኖችን ለመደምሰስ ብዙ አይሮፕላኖች በየጊዜው ቢዘምቱም ውጤት አላገኙም ።


"በደቡብና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ የተያዙት አምስት ከተሞች ብቻ ናቸው ። እነሱም ጅረን ፣ ይርጋ ዓለም ፣ ሜጋ ፣ ጐባና ጊኒር ናቸው ። ሌላዎቹ ክፍሎች ግን በአርበኞች እጅ ናቸው ። ......በጉራፈርዳ ፣ በጊሚራና በከፋ ያሉ ኢጣሊያኖች ተባረው ወጥተዋል ። ወደዚያም ለመሄድ መንገዱ አደገኛ ሆኖባቸዋል ። ባለፈው ወር የኢጣሊያ ጦር ከሐረር ወደ ጂጂጋ ሲሄድ አርበኞቹ በመንገድ ላይ ብዙ ጉዳት አደረሱበት ። ....ኢጣሊያኖቹ ደንከልና አውሳንም መያዝ አልቻሉም ።......" የሚል ዜና ነበር የወጣው ።




በዱሮ ትእዛዝ ታላላቅ መድፎች አርበኞች ወዳሉበት ሥፍራ ተወሰዱ ።




ታላላቅ መድፎች በአርበኞች ላይ ይተኰሱ ጀመር ።




በዱቼ ትእዛዝ ታላላቅ መድፎች አርበኞች ወዳሉበት ሥፍራ ተወሰዱ ።




ታላላቅ መድፎች በአርበኞች ላይ ይተኰሱ ጀመር ።




ደጃዝማች ገረሡ ዱኬ ።



አርበኞች ።



ግች ዘውዴ አስፋው (ከቀሪን ገረመው መጽሐፍ)




የጉጃም አርበኞች ።




ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ ።




ወይዘሮ ዘውዲቱ ግዛው (ከቀሪን ገረመው መጽሐፍ)



ፊታውራሪ ደስታ ሸዋ እርካብህ



ኃይለማርያም ማሞ ።




በቀለ ወያ




ደጃዝማች ዘውዴ ጥላሁን (ከቀሪን ገረመው መጽሐፍ)



ፊታውራሪ ወንድምነህ (ከቀሪን ገረመው መጽሐፍ)



ፊታውራሪ ከበደ ይርዳው በኢሉባቦር ከተማረኪ መሣሪያ ጋር (ከቀሪን ገረመው መጽሐፍ)



የአርበኞች ጉዞ ።



አርበኛው ፤ ዙርያዋን በሸቦ የታጠረችውን አዲስ አበባ ከተማን ከሩቁ ሲመለከታት ።





ሰውዬው !

## ፲፱፻፴፩—፲፱፻፴፬

ግራዚያኒ ተነስቶ ዱካ ዴ. አኦስታ ከተተኩና ለአስተዳዳሪነቱም ጀኔራል ናዚ ከተሾሙ በኋላ እልቂቱ በረድ እያለ ሄደ ። ናዚም በየቤተ ክርስቲያኑ እየዞረ መስቀል በመሳለምና ከሕዝቡ ጋር በሰላም በመደባለቅ ሰላማዊነቱን ለማሳየት ሞከረ ። ሙሉ በሙሉ ጦርነቱ ቆሞ ሰላም ሆንዋል አይባልም እንጂ ሁለቱ ዓመታት ካለፈው ጋር ሲተያዩ ሰላም የወረደባቸው ዘመናት መስለው ታዩ ። ኢጣሊያኖችም በያዙዋቸው ከተሞች ሆነው ሕዝቡን በመስበክ ተኩስ እንዲቆም የሚጥሩበት ጊዜ ነበር ። አብዛኛው የልማት ተግባር የተከናወነው በነዚህ ዘመናት ነበር ።

ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የኢጣሊያ ሲቢል ሠራተኞችና ኩባንያዎች በየቦታው ሥራ መክፈትና እርሻ ማረስ ጀመሩ ። 540 ኢጣሊያውያኖችም በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፋፊ የእርሻ ቦታዎችን ይዘው ማልማት ጀመሩ ። በተለይ በሸዋ ፡ በወገራ ፡ በጂማና በጨርጨር (ሐረርጌ) 113,760 ሔክታር ወይም 2844 ጋሻ መሬት በእርሻ አለሙ ። በእነኚህም የእርሻ ቦታዎች ላይ 3550 የኢጣሊያ ቤተ ሰቦች ሠፈሩ ።

ሁለት ቢሊዮን 700 ሚሊዮን ሊሬ ካፒታል ያላቸው 4007 ባለ እንዱስትሪዎች አነስተኛና መለስተኛ እንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ሥራ ጀመሩ ። አንድ ቢሊዮን አንድ መቶ ሚሊዮን ሊሬ ካፒታል የያዙ 4785 ኢጣሊያዊ ባለሱቆች ሱቆቻቸውን ከፈቱ ።

ወደ ኢትዮጵያ የሚገባው የኢጣሊያ ሠራዊት እየበዛ በመሄዱ ለማንኛውም በሽታዎች መታከሚያ የሚሆኑ ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች በየቦታው መሥራት ጀመሩ ። በጠቅላላው 25 ሆስፒታሎችን ሠሩ ። በ1931 ዓ.ም መጨረሻ ገደማ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ የሕክምና ዶክተሮች ብዛት ስምንት መቶ ደርሶ ነበር ። ኢጣሊያኖች ድል ሆነው በለቀቁ ጊዜ እንኳ የእንግሊዝ ጦር አዛዦች ከኢጣሊያኖች የተረከቡት የመድኃኒት ብዛት ሁለት ሚሊዮን ፓውንድ ዋጋ ያለው እንደነበረ ራሳቸው እንግሊዞች ጽፈዋል ።

በየከተማውና በየመንደሩ ሁሉ ሆቴል ቤቶች ተከፈቱ ። በአገሩ ሥራ አጥ የነበረው ኢጣሊያዊ ሁሉ በየመንደሩ ሆቴልና ቡና ቤት በመክፈት የደራ ገበያ ያገኝ ጀመር ። እንዲህ ዓይነቶችን መለስተኛ ሆቴል ቤቶችንና ቡና ቤቶችን ትተን ከፍተኛ የሆኑ 14 ሆቴል ቤቶች ተከፈቱ ።

9936 ኪሎ ሜትር ርዝማኔ ያለው የባቡርና የመኪና መንገድ ለመሥራት ፕላኑ ተጠና ። 6995 ኪሎ ሜትር ርዝማኔ ያላቸው መንገዶች ተሠርተው ተጠናቀቁ ። ከነዚህም መንገዶች ውስጥ 3422 ኪሎ ሜትር ርዝማኔ ያላቸው መንገዶች በአስፋልት የተሠሩ ነበሩ ። በመንገድ ሥራው በኩል ብቻ እንግሊዞች እንደገመቱት ከ80 እስከ አንድ መቶ ሚሊዮን ፓውንድ አውጥተዋል ።


የኢጣሊያ የሥራ ሚኒስትር ኮቦሊ ጂሊ ሲገልጡ “........በደንከል ውስጥ አቋርጦ የሚሄደው መንገድ ብቻ 175 ሚሊዮን ሊሬ ጨርሷል ። ጠቅላላ ሥራውም 7,460,000 እስኩየር ሜትር ሲሆን 34,000 እስኩየር ሜትር በአስፋልት የተሠራ ነው ። አራት ታላላቅ ድልድዮችና 1504 አነስተኛ ፋካዎች (ድልድዮች) አሉት ። መንገዱን ለመሥራት በመሀከለኛ ግምት 32,000 ሠራተኛ ተካፋይ ሆንዋል ። የመንገዱ ሥራ የተጠናቀቀው በ17 ሚሊዮን የሥራ ቀናት ነው ።....” በማለት ኮሪየሪ ዴል ሴራ ለተባለው ጋዜጣ መግለጫ ሰጥተዋል ።




መንገዶች ድንጋይ ተነጠፈባቸው ።




ገደሎች በዶማ ተናዱ ።




ጉቶዎች በዶማ ተፈለጡ ።




ብዙዎቹ መንገዶች ለአስፋልት ሥራ ተዘጋጁ ።



ገደሎች በሰው ልጅ ኃይል ተናዱ ።



የሰው ልጅ ኃይል



ያለዘመናዊ መሣሪያ በሰው እጅ ብዙ መንገዶች ተሠሩ ።

# የአዲስ አበባ እንደገና መያዝ

በሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም. የኢጣሊያ መንግሥት የጦር ጓደኛውን የጀርመንን ፈለግ በመከተል በእንግሊዝና በፈረንሣይ ላይ የጦር አዋጅ አውጆ በጦርነቱ ውስጥ መግባቱን ገለፀ ።

ጂማ የነበረ ፒሮቲ (Pierotti) የተባለ የኢጣሊያ አየር ኃይል ባልደረባ ኢጣሊያ ውስጥ ላለ ወዳጁ በጻፈው ደብዳቤ «.....በዚህ በታወጀው የጦርነት ወሬ አልተደሰትንም ። እኛ ለራሳችን ያለነው ጦርነት ውስጥ ስለሆነ ነው ።..... ጐጃም በሙሉ ሸፍቶ ይዋጋናል ። ዙርያችንን ጠላት ከቦ ይዋጋናል ።.....አዲሱ የጦር አዋጅ ምን ያደርጋል ?.....ታዛዦች ነንና እንዳዘዙን ለጦር ጓደኞች ሁሉ እንዋጋለን ።.....ሙሶሊኒ በኢጣሊያ ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ገብተው አያውቁም ። በዚህ በአፍሪካ የኢጣሊያ ግዛት ውስጥም ምን እንደሚካሄድ አላዩም ።.....» ብሏል።

እስካሁን ድረስ ለኢትዮጵያ ነፃነት አያስብ የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት አሁን እያሳሰበው መጣ ። ለማሳሰብም ያበቃው ሊቢያ ያለው የኢጣሊያ ጦር የእንግሊዝ የጅ አዙር ቅኝ ግዛት የነበረውን ግብፅን ከእንግሊዝ እጅ ለማስወጣት በመነሳቱ ፤ በምሥራቅ አፍሪካ ያለው የኢጣሊያ ጦር ደግሞ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች የነበሩትን ሱዳንን ፤ የእንግሊዝ ሶማሌንና ኬንያን ከእንግሊዝ ለማስለቀቅ በመወሰኑና ጦርነቱም በመጀመሩ ነበር ። በምሥራቅ አፍሪካ ያለው የኢጣሊያ ጦር በየአቅጣጫው ወሰን እየገፋ ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች መግባት ጀመረ ።የተበታተነው የእንግሊዝ ጦርም ኢጣሊያኖችን በኢትዮጵያውያን ለማስመታት ወሰነ ። ኢጣሊያኖች ግብፅን ፤ ሱዳንን ፤ ጂቡቲንና የእንግሊዝ ሶማሊያን ከያዙ ጠቅላላው ቀይ ባህር በቁጥጥራቸው ሥር ስለሚሆን ይህን አደገኛ አዝማሚያ በመገንዘብ እንግሊዞች ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር መሻረክ ጀመሩ ።

እንግሊዞች የኢትዮጵያን አርበኞች ለማቀፍና ለማበረታታት በአማርኛ ቋንቋ ተበታኝ ወረቀት አሳትመው በእንግሊዝ መንግሥት ስም የጀኔራል ፕላት ማኅተም እየተደረገበት ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ ተላከ ። ያም ወረቀት «....ሰላም ለእናንተ ይሁን ። እንግሊዝና ኢጣሊያ አሁን በጦርነት ላይ ናቸው ። ይህን የጋራ ጠላታችንን በተቻለ መንገድ ሁሉ ለማጥፋት እንድንችል በምንችለው ሁሉ ልንረዳችሁ ወስነናል ። ስለዚህ ጠመንጃ ፤ ጥይት ፤ ምግብም ሆነ ልብስ ቢያስፈልጋችሁ መልእክተኞችን ከሚነግራችሁ ድረስ ተረካቢ ሰውና መጫኛ እንስሳት ላኩ ። የጠየቃችሁትን ሁሉ እንልክላችኋለን ።....» የሚል ነበረ ከካርቱም የተበተነው ወረቀት ። ይህን ወረቀት የያዙም መልእክተኞች ጐጃም ፤ አርማጨሆ ፤ ወልቃይትና በጌምድር ላሉ አርበኞች አደረሱ ። በዚህ ጊዜ የኢጣሊያ ወታደሮች ከእንግሊዝ ሱማሌ በርበራ ፤ ከሱዳን ከሰላ ፤ ከኬንያ ሞያሌ ገብተው ነበር ።

እንግሊዞች በጠየቁት የጋራ ትብብር መሠረት የእንግሊዝ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ባሳተመው ዘ አቢሲኒያን ካምፓኝ የተባለው መጽሐፍ «.....የመሣሪያውን ዕርዳታ ለመጀመሪያ ጊዜ ከኛ ተቀብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ ላይ ያዋለው አንድ ዓይናው የቋራ ተወላጅ ግራዝማች ወርቁ ነው ። ኢጣሊያኖች ጋላባትን ይዘው ስለነበር የኢጣሊያ አሳሽ ቡድን (ፓትሮል) ጋላባት አካባቢ በሚዘዋወርበት ጊዜያን ጦር መታበት ።....» ሲል ያወሳል ።

በብዙ ሰዎች እምነት መሠረት ኢትዮጵያን ከኢጣሊያ ያላቀቃት እንግሊዝ ነው ይላሉ ። በኔ አስተያየት ግን አይደለም ። እንግሊዞች የደረሱት በምሥራቅ አፍ

ሪካ የነበሩዋቸው ቅኝ ግዛቶቻቸው በኢጣሊያኖች ከተያዙባቸው በኋላ እነኚያን
ቅኝ ግዛቶቻቸውን ለማስለቀቅ ነው ። ከዚያ በፊት ማለት ኢጣሊያ በእንግሊዞች
ላይ የጦር አዋጅ ከማወጇ በፊት ግን ከእንግሊዝ መንግሥት ዕርዳታ ለመጠየ
ቅና መሣሪያ ተቀብሎ በአርበኝነት ለመሠማራት ኬንያ ሄደው የነበሩ ኢትዮጵያው
ያኖች እየተያዙ ታስረዋል ። በምርኮኛነት መሠረትም በግዴታ በኬንያ ውስጥ
መንገዶችን እንዲሠሩ ተደርገዋል ። ኢጣሊያ ጦር ባወጀ ጊዜ ግን እነኚያን መን
ገድ ሰሪ አድርገዋቸው የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው እንዲ
ዋጉ ፈቀዱ ። ንጉሡም ከካርቱም በተነሱበት ጊዜ በብዙ ጭቅጭቅና ልመና ለኢ
ትዮጵያ ጦር የተሰጡት እንግሊዛውያን አንድ መቶ ወታደሮች ብቻ ነበሩ ። እን
ግሊዞች ቅኝ ግዛቶቻቸውን ለማስለቀቅ ከደቡብ አፍሪካና ከኒጀሪያ ያመጧቸው ወታ
ደሮች በኬንያና በእንግሊዝ ሶማሌ በኢጣሊያኖች የተያዙትን ግዛቶቻቸውን ካስ
ለቀቁ በኋላ ኃይላቸውን ከአርበኛው ጋር እያጠናከሩ ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ።

እንግሊዞች ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትም ምክንያት ኢትዮጵያን ከቅኝ ግዛቶ
ቻቸው ጋር ለመደባለቅ ነበር እንጂ ኢትዮጵያ ነፃ መንግሥት እንድትሆን ወይም
ንጉሱን በዙፋናቸው ለመመለስ አልነበረም ። ይህንንም እንግሊዞቹ ራሳቸው በግ
ልፅ ተከራክረውበታል ። ለምሳሌ በ33 ዓም ከኢጣሊያ በኋላ የመጀመሪያዎቹ ሰባት
ሚኒስትሮች ሲሾሙ የኢትዮጵያ መንግሥት የመሾም ሥልጣን እንደሌለው ከፍ
ተኛ ተቃውሞ አድርገዋል ። በመጨረሻ ከሰር ዊንስተን ችርችል ጋር በልመና ፣
ከውስጥ ደግሞ አርበኛው በያዘው ግዴታ መሠረት እርቅ ወርዶ ከአዋሽ በታች
ያለው አገር ማለት ሐረርጌ በሙሉ በጦር ማሳረፊያ ስም ለእንግሊዞች ተሰጠ ።
ያም አገር ከብዙ ክርክርና ድካም በኋላ ወደ ኢትዮጵያነቱ ተመለሰ ። ይህ ሁኔታ
ራሱ ቢዘረዘር ራሱን የቻለ አንድ መጽሐፍ የሚወጣው ስለሆነ ትቼዋለሁ ።

እንግሊዞች እኛ የመሣሪያ ዕርዳታ እንሰጣለንና እናንተ ተዋጉ ብለው ለአር
በኛው መልእክት በላኩ ጊዜ ደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ ለጀኔራል ፕላት በጻፉት
ደብዳቤ «.....ለፊታውራሪ ታፈሰ ዘለቀ የጻፉትንና በመተማ በኩልም የላኩልኝ
ደብዳቤ ደርሶኝ ተመልክቼው፥ በጣም ተደስቻለሁ ። አሁንም ብዙ ሰዎችና የጭ
ነት ከብቶች ልኬአለሁና ጠመንጃ ፣ ጥይትና በያይነቱ የጦር መሣሪያ ላኩልኝ ።
በመጨረሻው ጊዜም የእንግሊዝ መንግሥት ዕርዳታ በመላኩ እኛም የኢትዮጵያ
ጦረኞች ጠላታችን ኢጣሊያ የሚሄድበትን መንገድ ልናሳየው ነው ። እስካሁንም
ቢሆን እሷ ያለችው ባንዳንድ ቦታ በጥቃቅን መደበቂያ ውስጥ ተወሽቃ ነው ።...
እምበት ቀላል መድፍና አንድ መቶ መትረየስ ቢኖረን ጠላትን ፈጽሞ በአገራችን
ውስጥ አናስቀምጠውም ነበር ። ይህን ያልኩበት ምክንያት ከጠላቶቻችን በማረ
ክናቸው በለበንና በምንሸር ብቻ ያውም ጥይት እየቆጠብን እየተኮስን ጠላታችንን
ከአገራችን ማባረር አልቻልንም ።

«ባለን መሣሪያም ጠላታችንን አድክመናታል ። እንደወሬዋ ከሆነ ኢትዮጵ
ያውያኖችን ደምስሼ አገሪቱን እይዛለሁ ነው። አልቻለችም ።....የአገሪቱን ሩብ
እንኳ መግዛት አልሆነላትም ።.....ዳግመኛ ከመተማ በላይና ጐጃም ለሚያልፈው
ሁሉ በሩ እኔ ስለሆንኩ የኔን ፊርማ የያዘ ሰው ካልሆነ በስተቀር መሣሪያ አት
ስጡ ። ምክንያቱም ኢጣሊያኖች አስመስለው ሊወስዱ ይችላሉ ። ሶስተኛ ነገር
በበላያም ሆነ በየኮረብታዎቹ ያሉት የኔ ሰዎች ጠንካሮች በመሆናቸው ኢጣሊያ
ኢትዮጵያ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ሰዎቼን አልፎ ሊሄድ አልቻለም ። ስለዚህ....ከእ
ናንተ በኩል መልእክተኛ ይምጣና በላያ ውስጥ አይሮፕላን ማረፊያ ይፈልግ ።..."
በማለት መሣሪያ ካገኙ ሌላ እርዳታ እንደማይፈልጉ ገልፀዋል ። ይህም ቢሆን የእ
ንግሊዝ መንግሥት በጦርነቱ ያደረገውን አስተዋጽኦ ማርሳት የለብንም ። ጠቅላ
ለን ግን ከኢጣሊያ አገዛዝ ነፃ ያወጡን እንግሊዞች ናቸው ማለት ፈጽሞ አይቻ
ልም ።

ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያን የሚለቁበት ጦርነት በተነሳ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበራቸው ኃይል 3313 መትረየስ ፣ 5331 ፈጣን ተኳሽ ጠመንጃዎች (ግማሽ መትረየስ) ፣ 672.800 የተለያዩ ጠመንጃዎች ፣ 325 አይሮፕላኖች ፣ 994 መድፍና ሞርታር ፣ 6286 ሞተር ብስክሌቶችና መኪናዎች ፣ 7000 መኰንኖች ያሉበት 84.000 ኢጣሊያዊ ወታደሮችና ሁለት መቶ ሺ የቅኝ ግዛት ወታደሮች ነበሩዋቸው ።

በጎጃም በኩል ያለው ጦር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እንዴት አጅቦ ሸዋ እንደገባና እንዴትም እንደተዋጋ በየጊዜው በሰፊው ተጽፎለታል ። ስለዚህ በዚያ መስመር በኩል ያለውን የጦርነት ታሪክ ትቼ ወደ ምሥራቁ ጦር ግንባር ለማለፍ ፈለግሁ ። የምሥራቁን ጦር ግንባር የፈለግሁበት ምክንያት የኢጣሊያ ጦር ድል መሆኑን ያረጋገጠና ቀድሞ አዲስ አበባ በመግባት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አዲስ አበባ ውስጥ ያውለበለበ በመሆኑ ነው ።

እንግሊዞች ኬንያና እንግሊዝ ሶማሌ ውስጥ ለአገራቸው እንዳይዋጉ አስረው ያስቀመጡዋቸውን ኢትዮጵያውያንን መሣሪያ በመስጠት በእንግሊዝ ጦር አዛዦች ሥር ወደ ኢትዮጵያ እንዲዘምቱ አደረጉ ። ስሙና ስብከቱ ወደ ኢትዮጵያ ይባል እንጂ ኢትዮጵያውያኖቹ እንዲዋጉ በቅድሚያ የታዘዙት ኢጣሊያኖች የያዙዋቸውን የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት አገሮችን ማስለቀቅ ነበር ። ሁሉም ሆኖ ሁሉን አልፈው ኢትዮጵያ ውስጥ ገቡ ።

መጋቢት 8 ቀን 1933 ዓም የኢትዮጵያ ነፃ አውጭ ሠራዊት ጂጂጋ ገብቶ ጂጂጋ ከተማን ያዘ ።ኦጋዴን ውስጥ የነበሩ ኢጣሊያኖች በሙሉ ተሰባስበው ጂጂጋ ላይ ሠፍረው ነበርና የኢትዮጵያ ጦር አጥቅቶ ጂጂጋ በደረሰ ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ጂጂጋን ለቅቆ ካራመራ ላይ መሸገ ። በካራመራም መተላለፊያ በር ላይ ከባድ ውጊያ ከተደረገ በኋላ መጋቢት 12 ቀን የኢጣሊያ ጦር ካራመራን ለቅቆ በመሸሹ ካራመራ በኢትዮጵያ ጦር ተያዘ ።

ከካራመራ የወጣው የኢጣሊያ ጦር ባቢሌ ላይ ተጠናክሮ መሸገ ። ስለዚያን ጊዜው ሁኔታ አንድ የኢጣሊያ የጦር መኰንን በያዘው ማስታወሻ «.....መጋቢት ወር አጋማሽ፣ ጀምሮ ከጂዎችና የሚሸሹ በዙ ። ማርች 20 (በኛ መጋቢት 11) ቀን ማታ 38ኛው ባታሊዮን ተበታትኖ ከትእዛዝ ውጭ ሆነ ። የባታሊዮኑ መኰንኖችም ስለራሳቸው ብቻ መከላከል ጀመሩ ።39ኛው ባታሊዮን ተለይቶ ባቢሌ ላይ ሠፍሯል ፡ ባቢሌ ለሁለተኛ ጊዜ መከላከያ የወሰንናት ናት ። ባቢሌ ላይ ያሳለፍናቸው ቀናት በእርግጥ የችግር ቀናት ነበሩ ። በየምሽቱ የመኰንኖች ሕይወት በአደጋ ላይ ነበር ። በየምሽቱ ወታደሮቻችን እየከዱን ይሄዳሉ ። የሄዱትም እኛን ለማስፈራራትና ለማስጨነቅ ሌሊቱን ሙሉ ሲተኩሱብን ያድራሉ ።.......ከአራት ቀናት የጭንቅ ውሎ ማደር በኋላ ባቢሌን ለቀቅን ።........ባቢሌን ለቅቀን የወጣነው ሌሊት ነው ። ስንሔድም በሰላሳና በአርባ ሰዎች እየተከፋፈልን ነው ። አብረውንም ከኤርትራ የመጡ ወታደሮች አሉ ። እነኚህም እስከ መጨረሻው ታማኞቻችን ናቸው ብለን የምናስባቸው ነበር ። ግን በጉዞአችን ላይ ያለማቋረጥ ጠመንጃቸውን እየተኰሱና የጅ ቦምብ እየጣሉ ያሸብሩን ጀመር ። በዚህም ምክንያት በበቅሎ ላይ ተቀምጠን መሔድ አልቻልንም ። ምክንያቱም ከየአቅጣጫው ሁሉ የሚተኰሱት ጥይት በጆሮአችን አጠገብ እያፏጨ ስለሚያልፍ ነው ። የመኰንኖች ትዕዛዝ ተንቋል ። በዚህ ጊዜ ነው ውድቀታችንና ድል መሆናችንን የታወቀን ።.....

“ወደ ቀርሳ እንድንሸሽ ታዘዝን ።.......ጀኔራል ሳንቲኒ የሚያደርገውን አጣ ። ሕይወታቸውን ከአበሾች ለማዳን ከኛ ጦር ጋር የተደባለቁትን ኢጣሊያውያንና 400 የምንሆነውን ኢጣሊያውያን ወታደሮች በማዘዝ አሳቅ ላይ የገጠመንን ጦር ለሕይወታችን ስንል ሙሉ ቀን ተዋጋን ። ውጊያው ከአቅም በላይ ስለሆነብን ሌሊቱን እምልጠን ከዋናው ሠምድ በመግባት እጃችንን ለመስጠት ወሰንን ። በዚህም መሠረት ነጭ ባንዲራ ይዤ ሌሊቱን በሙሉ ተጓዝን ።.........” ብሏል ።

ሌላው የኢጣሊያ መኰንን ደግሞ በያዘው ማስታወሻ "......የሚከዳን ወታደር እየበዛ ሄደ ። በየዕለቱ ሌሊት ሌሊት የቅኝ ግዛት ወታደሮች ይከዱናል ። ወደ እንግሊዞች ይሂዱ ወይም ጫካ ይግቡ አይታወቅም ። .......ወር በገባ በ17ኛው ቀን ከጧቱ በ10 (በኛ 4) ሰዓት ከወንዝ አጠገብ ቆሜ ምክትል መቶ አለቃ ትሮያ (TROIA) በእጁ ጠመንጃውን እንደያዘ ወደኔ እየሮጠ መጣ ። ወዴት ትሄዳለህ? ብዬ ብጠይቀው አንድ አስከሪ (ጥቁር ወታደር) በዚህ በኩል ሮጦ ሲያልፍ አይተሃል ወይ? አለኝ ። እኔም ፣ ምን መሆንህ ነው? እነዚህ አስከሪዎች ሁል ጊዜ እንደሮጡና እንዳመለጡ አይደለም ወይ? አልኩት ። እሱም ይህ አስከሪ ሻለቃ ዜዛ (ZEZZA) ላይ የጅ ቦምብ ወርውሮ ገድሎታል ። እኔም የማባርረው ስለ ዚህ ነበር ። አሁንማ ወንዙን ተሻግሮ ሳይሄድ አይቀርም አለኝ ።....." ብሏል ።

መጋቢት 16 ቀን የኢትዮጵያ ነፃ አወጭ ጦር ሐረር ከተማ ገባ ። የሐረር ከተማ ሕዝብም ታላቅ የደስታ አቀባበል አደረገለት ። ከዚህም ጦር ለእገር ጥበቃ የሚቀረው ቀርቶ ሌላው ፣ የኢጣሊያን ጦር በመከታተል ወደ ድሬዳዋ ተጓዘ ። የኢጣሊያ ጦር ደንገጎ ተራራን ካለፈ በኋላ መንገዱን ሰባብሮት ስለነበር ጦሩ ከዚያ ሲደርስ ቆመ ። ተዋጊው ጦር መዋጋቱን ትቶ መንገድ መሥራት ያዘ ። የተሰበረው የደንገጎ መንገድ በ36 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ተሠርቶ እንዳለቀ ጦሩ ጉዞውን ቀጥሎ መጋቢት 20 ቀን 1933 ዓ.ም. ድሬዳዋ ገባ ።

ከድሬዳዋ ለእገር ጥበቃ የሚቀረው ቀርቶ ሌላው ፣ የኢጣሊያን ጦር በመከታተል ወደ አዋሽ ተጓዘ ። የኢጣሊያ ጦር የአዋሽ ወንዝን ከተሻገረ በኋላ የባቡሩን ሐዲድ ድልድይና ለመኪና መሻገሪያ ተሠርቶ የነበረውን ድልድይ ሁለቱንም በፈንጅ አፍርሶ ስለነበረ የኢትዮጵያ ጦር ከዚያ ሲደርስ ቆመ ። የኢጣሊያ ጦርም ለመጨረሻ ውጊያ አዋሽ ወንዝን አልፎ መሽጎ ነበር ። የኢትዮጵያ ጦር አዋሽ ወንዝን ለመሻገር አስቸጋሪ ሆኖ ስላገኘው እንደተለመደው ውጊያውን አቁሞ ድልድይ መሥራቱን ያዘ ። ድልድዩን በሚሠራበት ጊዜ ባሻጋሪ መሽጎ የነበረው የኢጣሊያ ጦር ምሽጉን ጥሎ ሸሸ ። የኢትዮጵያ ጦርም ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ድልድዩን ሠርቶ ጨረሰ ። በሠራው አዲስ ድልድይ ጦሩ ወንዙን ተሻግሮ ዐሐይዋ ፍንጥቅ ስትል አዋሽ ከተማ ገባ ። አዋሽ እንደገባም የኢጣሊያ ጦር ወደ አዳማ ወደ ዛሬው ናዝሬት መሸሹ ተነገረው ። ከዚያም ክትትሉን ቀጥሎ አዳማ ደረሰ ። የአዳማ የዛሬው ናዝሬት ሕዝብም የኢትዮጵያን ጦር በታላቅ አቀባበል ተቀብሎ የኢጣሊያ ጦር ወደ ሞጆ ማለፉን ተናገረ ።

ይህ የኢትዮጵያ ጦር በሚጓዝበት ጊዜ በየቦታው የሚያገኘው ድልና የሚማርከው ምርኮም መሣሪያ በጣም የበዛ ነበር ። የ22ኛው የምሥራቅ አፍሪካ እግረኛ ብርገድ አዛዥ የነበሩት እንግሊዛዊው ጀኔራል ፎውኪስ "......25,000 ኢጣሊያኖች ፣ 85 መድፎች ፣ 11 ታንኮች ፣ ለቁጥር ያታከቱን መትረየስና ጠመንጃዎችን ማረክን ። ግሩፓችንም 12 የኢጣሊያ ጀኔራሎችና ብዙ የኢጣሊያ መኰንኖች ተጨመሩበት...." በማለት ጽፈዋል ።

የኢትዮጵያ ጦር የኢጣሊያን ጦር በመከታተል ወደ ሞጆ ተጓዘ ። ሞጆ ከተማ ለመግባት አምስት ማይል ያህል ሲቀረው በሞጆ ከተማ ከባድ ተኩስ ስለነበር ጦሩ ከሞጆ አምስት ማይል ከራቀ ቦታ ሠፈረ ። በኋላ በሰላዮች እንደተረጋገጠው ተኩሱ የሚተኮሰው ከጠላት ወገን ሳይሆን የከተማው ሕዝብ በከንቱ በፍዶ ሜዳ የሚያስጮኸው መሆኑ ታወቀ ።

አሁን አዲስ አበባ እንግባ ። እስቴር እንደጻፈው "........ኢጣሊያኖች አዲስ አበባ ከተማን ለመቆጣጠር አልቻሉም ። የሚተማመኑባቸው ባለጥቁር ሸሚዞችን ነብሰበላ ነጩን ሠራዊት እንዲጠብቁ አደረጉ ።......" ይላል ።

እ.ኤ.አ. ማርች 22 ቀን 1941 ዓ.ም. የወጣው ዴይሊ ቴሌግራፍ ጋዜጣ ሲጽፍ '.......የኢጣሊያ ሰዎች የፈረንሳይ ግዛት ወደ ሆነችው ወደ ጅቡቲ በመሸሽ ላይ ናቸው ። ምክንያቱም በአዲስ አበባ አካባቢ ከአሥር ሺ እስከ 15,000 የሚሆኑ

የኢትዮጵያ አርበኞች በመጠናከራቸው ማታ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ በመኪና መሄድ አይቻልም ። ቀንም ቢሆን በአጃቢ ነው ከከተማው የሚወጣው……” ብሏል። ቤርክባይ ደግሞ “………ማንኛውም ኢጣሊያዊ ሣምንት ሙሉ ከዋናው ከተማ ውጭ ባለው መንገድ መጓዝ አይችልም ነበር ። በከተማው ዳርቻ ያሉ መንደሮች ሁሉ በአርበኞች ወይም በሽፍቶች ተይዘዋል ። ማምቢሬኒ በአዲስ አበባ ከተማ ስለሚሆነው መተራረድ ፈርቷል ። ከሣምንት በፊት እንደደረስን በአዲስ አበባ ዙርያ 35 ምሽግ ተሠርቷል ። ከእነኚህም ሌላ ሰባት የተለዩ ምሽጐች ተሠርተዋል ። ምሽጐቹ ሁሉ እሾሃማ በሆነ የሽቦ አጥር ተገናኝተዋል ። ሚያዝያ 4 (በኛ መጋቢት 26) አንድ መግለጫ ወጣ ። መግለጫው ኢትዮጵያውያን ጦርነት ሲያነሱ ለአሥር ደቂቃ የሚቆይ ሴረን ይነፋልና ሴቶችና ሕፃናት በተዘጋጀው የመሸሸጊያ ቦታ ሁሉ እንዲገቡ የሚል ነበር ። በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በግንብ የተሠራው የመሸሸጊያ ቦታ ሁሉ በካርታ ተዘጋጅቶ በግልጽ ይታወቃል ። እንደ አልቤርጐ ኢምፔሪያሌ የመሳሰሉት ደግሞ ዙርያ ክባቸውን በእሾካማ ሽቦ ታጥረዋል …..” ብሏል ።

ቤርክባይ እንደፃፈው “……ሚያዝያ 3 ቀን (እ.ኤ.አ.) ከፈረሰኛ ሬዥሜንት ምርጥ የሆኑ 450 ወታደሮች ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ በአዲስ ዓለም መንገድ ያሉትን ሽፍቶች ቦታቸውን ለማስለቀቅ ተላኩ ። አርበኞቹም ድንገት ከመንገድ ላይ አቋርጠዋቸው 50 ሰዎች ድነው ሲመለሱ ሌሎችን ፈጇዋቸው……” ይላል ። ከዚህ እልቂት በኋላ ነው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሴረን ሲጮህ ነጩ ሕዝብ ወደ ተዘጋጀው ዋሻ እንዲገባ መግለጫ የወጣው ።

በዘመኑ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የነበረው የደቡብ አፍሪካው ተመልካች ኢሪክ—ሮሲንታል እንደገለፀው “…..አርበኞቹ አዲስ አበባ ሲገቡ በሰይፍ እንደሚያርዷቸውና ቤታቸውንም እንደሚያቃጥሉባቸው እያሰቡ ኢጣሊያኖቹ ፍፁም በሆነ ፍርሃት ተውጠዋል ። በየቦታው ምሽጐች ተሠርተዋል ። ከተማዋ በእሾሃማ ሽቦ ዙሪያዋን ታጥራለች ።……የመንግሥት ሕንፃዎችና ጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ሁሉ በሽቦ ታጥረዋል ። አንዳንድ መንገዶችም ሕዝብ እንዳይተላለፍባቸው ተዘግተዋል .።………” ብሏል ።

እንዲህ ሆኖ ሳለ በምሥራቅ በኩል የመጣው የኢትዮጵያ ጦር እየገፋ አዲስ አበባ አካባቢ ደረሰ ። በጄኔራል ዊዘሮል የሚመራው ጦር ለአዲስ አበባ ከተማ 20 ኪሎ ሜትር ያህል ሲቀረው አቃቂ ላይ ሠፈር አደረገ ። ጦሩ አቃቂ ላይ ሠፈር ያደረገው በማግሥቱ አዲስ አበባ ለመግባት አስቦ ነበር ።


አቃቂ ላይ ሠፈር አድርጐ ያደረው ጦር መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም. ከአቃቂ ተነስቶ ጉዞውን ወደ አዲስ አበባ ከተማ አመራ ። ጦሩ ወደ አዲስ አበባ በሚያመራበትም ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ የነበሩ የኢጣሊያ ምርጥ ወታደሮች ጦሩ በሚያልፍበት መንገድ ግራና ቀኝ በሰልፍ ቆመው ለጦሩ ሰላምታ በመስጠት የሰላም አቀባበል አደረጉ ። በተለይ የኢጣሊያ ባለ ሞተር ብስክሌተኞች በሞተር ብስኪሊቶቻቸው ሆነው ጦሩን እየመሩ አዲስ አበባ አገቡት ።

የእንግሊዝን ባንዲራ እያውለበለበች ቀድማ ትጓዝ የነበረችው የእንግሊዝ ብረት ለበስ መኪናም በቀጥታ የናዚ ቢሮ ከነበረው ከዛሬው ዩኒቨርስቲ ሄደች ። ከዚያ እንደደረሱም በጄኔራል ማምቢሬኒ የሚመራ የኢጣሊያ ወታደር በሰልፍ ተቀበላቸው ። አርባ ጫማ ርዝማኔ ካለው ብረት ላይ ይውለበለብ የነበረው የኢጣሊያ ባንዲራ ወርዶ በቦታው የእንግሊዝ ባንዲራ ተተካ ። ይህ ሥነሥርዓት ከተፈፀመ በኋላ ጉዞው ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ማለት ወደ ምኒሊክ ቤተ መንግሥት አመራ ። ከታላቁ ቤተ መንግሥት ሲደርሱ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቅሎ ጄኔራል ዊዘሮል ንግግር አደረጉ ። በንግግራቸውም “……ይህ ቀን ለኔ የምኮራበት ቀን ነው……”አሉ ።

ይህ በምሥራቅ በኩል የመጣው ጦር በ53 ቀን ውስጥ 1725 ማይል መንገድ ተጉዞ አዲስ አበባ ገብቶ የኢጣሊያን አውርዶ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይሰቀል እንጂ በየቦታው ውጭ ውጭውን ያለው ጦርነት ገና አልቆመም ነበር ።



ጀኔራል ዊንጌት የኢትዮጵያውያንን ሰልፍ ሲጎበኙ ።




የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ከመሬት እንዳሉ ተደበደቡ ።




ሜጋ ላይ የተማረከው 600 የኢጣሊያ ሠራዊት ።



በአዲስ አበባ የተማረከው ጠመንጃ ቁልሉ አሥር ሜትር ውፍረትና 200 ሜትር ርዝማኔ ነበረው ።




በምድር ውስጥ ተቀብረው የነበሩ ፈንጂዎች እየተቆፈሩ ወጡ ።



በአቀርዳት የነበሩ የኢጣሊያ አይሮፕላኖች በሀንጋራቸው ውስጥ እንዳሉ ተቃጠሉ ።




ከኢጣሊያ የተማረኩ ቀላል ታንኮች ።




ከኢጣሊያ የተማረኩ ታላላቅ መድፎች




በእንግሊዝ የሚታዘዘው የ10ኛው የሕንድ እግረኛ ወታደር የአትባራን ወንዝ ሲያቋርጥ ።



የአዲስ አበባው አይሮፕላን ማረፊያ በእንግሊዞች ቦምብ ተደብድቦ 32 አይሮፕላኖች ተቃጠሉ ።



የእንግሊዝ ሠራዊት ሐረር ከተማ ለመግባት ሲጓዝ ።




ኢጣሊያኖች የአዋሽን ድልድይ ከሠበሩት በኋላ በአንድ ቀን ተመልሶ የተሠራው ጊዜያዊ ድልድይ።




ኢጣሊያኖች ሲሸሹ የአዋሽን ድልድይ በዚህ ዓይነት ነበር የሰበሩት።



አዲስ አበባን ለመያዝ ለሚገሰግሰው የኢትዮጵያ ጦር ናዝሬት (አዳማ) ላይ የተደረገለት አቀባበል።




ኢጣሊያኖች እጃቸውን ለመስጠት ሲጠባበቁ ።




የምሥራቁ አርበኛ ከእንግሊዞች ጋር ወንዝ እያቋረጠ ሲገዝ ።




በአቃቂ ከተማ የምሥራቁን የኢትዮጵያን ጦር ለመቀበል የሚጠባበቀው የኢጣሊያ ሠራዊት ።



በታላቁ የዳግማዊ ምኒልክ ቤተ መንግሥት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀል።



የዱካ ዲ. አኦስታ ወታደር ከምሽጉ ሲወጣ የእንግሊዝ ወታደር በሰልፍ ተቀበለው ።



በአምባላጌ የነበረው የኢጣሊያኖች (የዱካ ዲ. አኦስታ) ምሽግ ።



ዱካ ዲ. አኦስታ በእንግሊዝ ተይዞ ሲሔድ ።



ጄኔራል ቶሴሊ የነበረበት ምሽግ ፍርስርሱ ወጥቶ ተያዘ።

# የጦርነቱ ፍጻሜ

በነሐሴ ወር 1933 ዓም እንግሊዞች ባወጡት መግለጫ«...ኢጣሊያ ጦርነ
ቱን ስትጀምር በምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ 125.000 ኢጣሊያውያን ፣ 200.000 አፍ
ሪካውያን ወታደሮች ነበሩዋት ። ከዚህ ውስጥ አንድ መቶ ሺ ኢጣሊያውያን ማር
ከናል ። 6.000 ኢጣሊያውያን ገና በጦርነት ላይ ናቸው ። ከዚያ የቀሩት ሌሎች
ግን ሞተዋል ። ከሁለት መቶ ሺ አፍሪካውያን ወታደሮች መካከል ሰላሳ ሺውን
ማርከናል ። ከጥቂቶች በስተቀር ሌላው አፍሪካዊ ወታደር ኢጣሊያን እየከዳ ኢጣ
ሊያን በመውጋት ላይ ነው ። ከጦር መሣሪያዎችም 800 ታላላቅ መድፎች ፣
በብዙ ሺ የሚቆጠሩ መትረየሶች ፣ 150 ታንኮችና በሺ የሚቆጠሩ መኪናዎች
ማርከናል ።.....

«አሥመራ ካለው ካንድ የጦር መሣሪያ መጋዘን 1.500.000 የመድፍ ጥይት ፣
300.000 የጠመንጃ ጥይት አግኝተናል ። ከኢጣሊያ ሶማሌ ውስጥም 3.500.000
የጠመንጃ ጥይት ማርከናል ። ጦርነቱን ስንጀምር ኢጣሊያ 212 ቦምብ ጣይና
በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሌሎች አይሮፕላኖች ነበሩዋት ። ከጃንዋሪ 19 ቀን እስከ
አፕሪል 7 ቀን ድረስ 42 ቦምብ ጣይና 28 ተዋጊ አይሮፕላኖችን ጣልን ። ሌላዎ
ቹን ግን በየማረፊያ ሜዳቸው ላይ እንዳሉ መታናቸው ።.....» ብለዋል ።

አሸናፊ ማብዛት ተሸናፊ መቀነስ የተለመደ ነገር ስለሆነ የኢጣሊያ ጦር ሚኒ
ስቴር ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ ባወጣው መግለጫ «.....በኢትዮጵያ ውስጥ በተካሄ
ደው ጦርነት 426 ኢጣሊያዊ መኰንኖችና 4785 ኢጣሊያዊ ወታደሮች ሲሞቱ
በቅኝ ግዛት ወታደሮች በኩል የሞቱት 10.000 ወታደሮች ናቸው ። 703 ኢጣሊ
ያዊ መኰንኖችና 6244 ኢጣሊያዊ ወታደሮች ሲቆስሉ ከቅኝ ግዛት ወታደሮች የቆ
ሰሉት 16.000 ናቸው .....» ብለዋል ።

የኢትዮጵያ ድል አድራጊ ጦር አዲስ አበባን በያዘበት ጊዜ በአዲስ አበባ
ውስጥ 38.882 ፣ በአስመራ 49.139 ፣ በሐረር 4265 ፣ በጂማ 5283 ፣ በድሬዳዋ 3542
በጐንደር ሁለት ሺ ኢጣሊያኖች ነበሩ ። እነኚህም ሰላማዊ ሆነው በሰላም እጃቸ
ውን የሰጡ ናቸው ። ሌላው ግን በየቦታው እየመሸገ ውጊያውን ቀጥሏል ። የሙ
ሶሊኒ እንደራሴ የነበረው ጀኔራል ናዚ በጐንደር ፣ የኢጣሊያው ንጉሥ እንደራሴ
ዱካ ዲ አኦስታ ደግሞ በአምባላጌ መሽገው ከባድ ችግር ፈጥረው ነበር ።

አዲስ አበባ ከተያዘ በኋላ ጐንደር የመሸገውን የኢጣሊያ ሠራዊት ለማስለ
ቀቅ ወደ ጐንደር የተላከው የኢትዮጵያ ሠራዊት ቁልቋል በር ሲደርስ በዚያ የመ
ሸገው የኢጣሊያ ሠራዊት ተኩስ ከፈተ ። ኢጣሊያኖችም ጐንደርን ላለመልቀቅ
ጠንክረው ተዋጉ ። በዚያም ቦታ 513 ወታደር ሞቶባቸው 404 ወታደሮች ቆስሉባ
ቸው ። ከዚህ በኋላ ኢጣሊያኖቹ አፈግፍገው ጐንደር ከተማ አካባቢ በተደረገው
ውጊያ 517 ወታደሮች ከተገደሉባቸው በኋላ ኢጣሊያኖች ድል ሆነው ጐንደር
ከተማ ተያዘ ።

የኢጣሊያ ጦር አዝማች የነበረው በጐንደር የመሸገው ጀኔራል ናዚ ከዚህ
ውጊያ ቀደም ብሎ ለኢጣሊያ ጦር ሚኒስቴር በላከው ሪፖርት «...ወታደሮቻ
ችን ተጐሳቁለዋል ። ልብሳቸውም ተቀዳደዷል ። አብዛኛዎቹ ጫማ አልቆባቸው
ባዶ እግሮቻቸውን ናቸው ። ደሞዛቸውንም በጊዜው መክፈል አልቻልንም ። ያለን
የጦር መሣሪያም አኩሪና በቂ አይደለም ። ታንኮቻችን ታንክ ተብለው የሚጠሩ

ከሆነ የቀሩን የማይረቡት ናቸው ። መድፎቻችን ከጊዜው ውጭ ሆነዋል ። ጠመን ጃዎቻችን የተሰባበሩ ናቸው ። የጥይትም እጥረት አለብን ። በመጋዘን ያሉን ጥይ ቶች የተበላሹ ናቸው ። ከሶስት ሁለቱ የማይተኮስ ነው ። የአይሮፕላን መከላከያ መሣሪያ የለንም ። ያሉንም መኪናዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው ።....የምንበላውም የሻገተ ቂጣ ነው ።.....ሰዎቻችን ትንባሆዋቸው አልቆባቸዋል ። ከቤተሰብ የሚ ደርሳቸውም ደብዳቤ ተቋርጧል ። .....በጠላት ተከበናል ። ዙሪያችንንም ኢትዮጵ ያውያን ሽፍቶች ይዘውታል ። .....» ብሎ ነበር ።

እምባላጌ የመሸጉት ዱካ ዲ አኦስታ ደግሞ አዲስ አበባ ከተያዘ በኋላ ተጋ ትረው ይዋጉ ጀመር ። ዱካ ዲ አኦስታ የየዕለቱን የጦርነቱን ሁኔታ ይመዘግቡ ነበር ። ያ የማስታወሻ ደብተራቸው በኋላ ጊዜ ታትሞ ለሕዝብ ተገልጿል ። ባጭሩ ብንመለከተው እንዲህ ይላል ።

«ግንቦት 7 ቀን ። የውጊያው ይዞታ እየባሰብኝ ሄደ ። በሕክምና አሰጣጡ ተግባርም የማደርገው ነገር ጠፋኝ ። ገና ሲጀመር 50 ሰዎች ሞተውብኝ 150 ሰዎች ቆስለውብኝ ነበርና ነው ።

«ግንቦት 8 ቀን ። የእንግሊዝ አይሮፕላኖች የሚጥሉት ቦምብ እየከፋ ሄደ ። ጭሱ ለመተያየት እንኳ እንዳንችል አድርጎናል ። የጠላት ጦር ወታደሮች ከዋሻችን በር ድረስ ደርሰዋል ። በኛ በኩል ያለው ጦር ምንም ሳይቀንስ እንዳለ ተጋፍጧል። ይህ ሁሉ ሲሆን በሚዋጉት ወታደሮች መሐል ሆኜ ብዋጋ እደሰት ነበር ። ቀደም ብሎ መሞት ደግ ሲሆን ሳይሰሩ መገኘት ደግሞ የዚያኑ ያህል ከከፉ አጋጣሚ ይጥላል ።

«ግንቦት 9 ቀን ። ፖስቴሊዮኒ በጣም ቸኩሏል ። ዛሬ ማታ ከእምባላጌ ለቅቀን እንድናፈገፍግ ነግሬው ነበር ። በዚህ ቀን የእምባ ጉንጯን መታኮሻ በር መልቀቅ ግድ ሆነብኝና ለቀቅሁ ። በማንኛውም በር በኩል መፈናፈኛ እስካጣ ተዘ ጋብኝ ። በዛሬው ዕለት ሲወርድብን የዋለው የመድፍ ፣ የመትረየስና የጠመንጃ ጥይት እጅግ በጣም የበዛ ነበር ። መድፈኞችም የሚተኩሱት ጥይት ባለ 81 ፣ ባለ 114 እና ባለ 152 ነበር ።

«ግንቦት 10 ቀን ። 200 የሚሆኑ ያገር ተወላጅ ወታደሮች ከድተውኝ ጠፉ ። የእንግሊዞች አየር ኃይል የሚጥለው ቦምብ ሠራዊቱን አስመርሮታል ። ሠራዊቱ ተሰላችቷል ። የዛሬዋ ዕለት ዐጥ ያለች ብትሆንም 500 የመድፍ ጥይት ተተኩ ሶብናል ። 5 እና 6 ሰዓት የሚሆን ያህል በራሳችን ላይ ጥይት እያፏጨብን አል ፏል ። የእንግሊዝ አየር ኃይል ምሽጋችንን እያነጣጠሩ ምሽጉን በቦምብ ሲደበድቡ ውለዋል ።

«ግንቦት 11 ። ዛሬ ጠላት ከ3000 የሚበልጥ የመድፍ ጥይት ሲተኮስብን ዋለ ። በአቅራቢያዬ ይገኙ የነበሩትም ሁለት የመታከሚያ ቤቶች ባገሩ ተወላጅ ድርጅቶች ተወሰዱብኝ ።

«ግንቦት 12 ። ጠላት በብዙ ስፍራ ገጥሞን ነበር ። በመልስ ውጊያችን ወደ ኋላው እንዲያፈገፍግ አድርገነው ዋልን ። ከሰዓት በኋላ ኢትዮጵያውያን ማጥቃት ጀመሩ ። እነሱም እየሮጡ ሲመጡብን ያስፈራሉ ። ይዋጉናል ። ግን ገፍተው ሥፍራ አላስለቀቁንም ። በዛሬው ቀን በትእዛዜ ውስጥ ያለውን የተረፈውን ሰውና የጦር መሣሪያ ቆጠርሁ ። 4000 ወታደሮች ፣ 36 ባለ 75ና ባለ 65 መድፎች ነበሩኝ ። ሥራው እምብዛም የማያስደስት ቢሆንም ምንም የለበትም ግድ የለም ።

«ግንቦት 13 ቀን ። ቁስለኞች በዝተውብን ነበር ። ምንም ላደርግ ባለመቻሌ ግራ ገብቶኝ ዋለ ። የሠራዊቱም ንግግር ሕሊናዬን ከሚወቅሰኝ ደረጃ ደረሰ ። ድል

የመሆናችንን ጊዜ መቃረቡንና በእርዳታወም በኩል ያለመላካቱን እያስታከኩ ሲያ ጉረመርሙብኝ ዋሉ ።

«ግንቦት 14 ቀን ። የመጣው ቢመጣ ከዚች ሥፍራ አልወጣም ።

«ግንቦት 15 ። ትልቅ ውጊያ ነበር ። ምሽጉን አጠናክረው ከያዙልን ሰባት መቶ ሰዎች ውስጥ 170 ሰው ብቻ ተረፈኝ ። የቀረው አለቀ ። ወታደሮቼም ደክመው ዋሉ ። ቁስለኛው እየበረከተ ሄደ ። ነኢትዮጵያ ዓይነተኛ የታሪክ መዝገብ የሚከፈትበት ቀን የቀረበ መሰለኝ ።

«ግንቦት 16 ቀን ። 18 ቀን ሙሉ ያደረግነውን ጦርነት አስብኩ ። በሰላሳ ሺህ የመድፍ ጥይት ተደብድበናል ። ይህ ሁሉ የመድፍ ጥይት በጥቂት ቦታ ላይ እየ ተደራረበ ያረፈብን ነው ። እኔም ከመጨረሻው ቦታ ላይ መድረሴ ተሰማኝ ።

«ግንቦት 17 ። ዛሬ ጄኔራል ትሬቢኒ የእርቅ ድርድር መነጋገር ጀመረ ። እኔም ከምሽጉ ውስጥ ወታደሮቼ ሁሉ ወጥተው ካለቁ በኋላ ወጥቼ የሚመጣውን ለመ ቀበል እንድችል ተደረገ ። ስወጣም በብረት የክብር ሰላምታ ይቀርብልኛል ። በው ስጡ የነበሩት ወታደሮቼና ታማኝ የነበሩት የአገር ተወላጅ ወታደሮች በአንድ በአነስተኛ ጦር እየተመሩ ሲያልፉ ተሰልፎ የነበረው የጠላት ዘብ በብረት የክብር ሰላምታ ይሰጥ ነበር ።

«ግንቦት 18 ቀን ። ከምሽጉ ውስጥ ገና ሳልወጡትና ለቆሰሉ ወታደሮች ድን ኳኖች እንዲተክሉላቸው አደረግሁ ።

«ግንቦት 19 ቀን ። የጠላት ወታደሮች ተሰልፈው ፣ ሙዚቃው እየተመታ የኛ ወታደሮች ሲያልፉ ጠብ የነበረበት ሜዳ አይመስልም ነበር ። የአምባላጌው ምሽግ ባዶውን ቀረ ።

«ግንቦት 20 ቀን ። ከአምባላጌ ምሽግ ውስጥ ለቅቄ ራቤን ቀና አድርጌ በሀገሬ ወታደሮችና በጠላቴ ፊት ተራመድሁ ። ከዚያም አለፍ ብዬ በማጆር ቶዜሊ ስም በቆመው መታሰቢያ አጠገብ እንደደረስሁ ጄኔራል ሜይንና ብርጋዲየር ማሪየትን አገኘኋቸው ...» ይላል ። ዱካ ዲ አኦስታ ከተማረኩ ከሶስት ወር በኋላ ናይሮቢ ወታደር ሆስፒታል ገብተው ሞቱ ።

በዚህ ሁኔታ የሁለቱ ታላላቅ ሽፍቶች ወይም ወንበዴዎች ሁኔታ ተፈፀመ ። ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ የኢጣሊያ መንግሥት ላደረሰው ጥፋት ካሣ እንዲከፍላት ጠየቀች። ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠየቀው ካሣ 185 ሚሊዮን ፓውንድ እስተርሊንግ ወይም 326 ቢሊዮን ሊሬ ነበር ። በመጨረሻ በተደረገው ስምምነት የካሣው ገንዘብ 6.250.000 ፓውንድ እስተርሊንግ ወይም 10 ቢሊዮን ተኩል ሊሬ እንዲሆን ተወሰነ ።

በኢትዮጵያ መንግሥት የተጠየቀው ካሣ እንደሚከተለው ነበር ።

| | |
|---|---|
| ለጦር መሣሪያ የወጣ ... ... ... ... ... ... ... | 26.813.155 ፓውንድ |
| ባምስቱ ዓመት የቀረ የግብር ገቢ ... ... ... ... | 25.402.868 ፓውንድ |
| ለተለያዩ ክሣራዎች ... ... ... ... ... ... ... | 132.530.000 ፓውንድ |
| ድምር ፦ ... ... ... ... | 184.746.023 ፓውንድ |

ነበር ።

ለጦር መሣሪያ የወጣ የሚለው ሲዘረዘር

| | |
|---|---|
| ሀ/ ለ365.000 ወታደሮች መሣሪያ ... ... ... ... | 3.650.000 ፓውንድ |
| ለ/ ለጠመንጃና ለጥይት | 3.513.155 » |
| ሐ/ ለማጓጓዣ | 9.125.000 » |
| መ/ ላንድ ወታደር 3 ፓውንድ ሂሳብ የ10 ወር ደሞዝ | 10.450.000 » |
| ሠ/ ለጠፉ 15 አይሮፕላኖች ዋጋ ... ... ... ... ... | 75.000 ፓውንድ |
| ድምር ፡— | 26.813.155 ፓውንድ |

ለተለያዩ ከሣራዎች የሚለው ደግሞ ሲዘረዘር፡—

| | |
|---|---|
| ለተቃጠሉ ሁለት ሺ አብያተ ክርስቲያናትና ቅርሶች | 2.000.000 ፓውንድ |
| ለተቃጠሉ 525.000 ቤቶች | 10.500.000 ፓውንድ |
| በጦርነት ለሞቱ 275.000 ወታደሮች የደም ዋጋ ... ... | 27.500.000 ፓውንድ |
| ባምስቱ ዓመት ለሞቱ 78.500 አርበኞች የደም ዋጋ ... ... | 7.850.000 ፓውንድ |
| ባምስቱ ዓመት ለሞቱ 17.800 ሴቶችና ሕፃናት ... ... | 1.780.000 ፓውንድ |
| በየካቲት 12 ላለቁት ሠላሳ ሺ ሰዎች ... ... ... ... | 3.000.000 ፓውንድ |
| ተማርከው ለተገደሉ 24.000 አርበኞች ... ... | 2.400.000 ፓውንድ |
| እየታሰሩ ለሞቱ 35.000 ሰዎች ... ... ... ... ... | 3.500.000 ፓውንድ |
| በስደትና በረሃብ ለሞቱ 300.000 ሰዎች ... ... ... | 30.000.000 ፓውንድ |
| ለአምስት ሚሊዮን የቀንድ ከብቶች እልቂት ... ... ... | 25.000.000 ፓውንድ |
| ለሰባት ሚሊዮን በጐችና ፍየሎች እልቂት ... ... ... | 7.000.000 ፓውንድ |
| ላንድ ሚሊዮን ፈረስና በቅሎዎች ... ... ... ... ... | 5.000.000 ፓውንድ |
| ለ700.000 ግመሎች ... ... ... ... ... ... ... | 7.000.000 ፓውንድ |
| ድምር፡— | 132.530.000 ፓውንድ |

| | |
|---|---|
| ሂሳቡ የታሰበው ለአንድ ቤተ ክርስቲያን | 1000 ፓውንድ |
| » ቤት | 20 ፓውንድ |
| » ሰው | 100 ፓውንድ |
| » የቀንድ ከብት | 5 ፓውንድ |
| » በግ ወይም ፍየል | 1 ፓውንድ |
| * ፈረስ ወይም በቅሎ | 5 ፓውንድ |
| » ግመል | 10 ፓውንድ ነበር ። |

ተፈፀመ

# ዋቤ መጻሕፍት

## የዚህ መጽሐፍ ታሪክ የተለቀሙባቸው መጽሐፍት ዝርዝር


| የደራሲው ስም | የመጽሐፉ ስም |
|---|---|
| ደጃዝማች ከበደ ተሰማ | የታሪክ ማስታወሻ |
| አቶ ሞገስ ከፍሌ | የሙሶሊኒ ምስጢር |
| ALESSANDO LESSONA | MEMORIE |
| ANGELO DEL BOCA | THE ETHIOPIAN WAR, |
| CESCO TOMASELLI | CON LE COLONNE CELERI |
| CIRO POGGIALI | DIARIO AOI |
| CORRADO ZOLI | IL PRIMO ANNO DELL'EMPERO |
| E.CANEVARI | GRAZIANI MI HA DETTO |
| EMILIO DE BONO | ANNO XIII |
| EVELYN WAUGH | REMOTE PEOPLE |
| E.W. POLSON NEWMAN | THE NEW ABYSSINIA |
| FIDENZIO DALL'ORA | INTENDENZA IN A.O. |
| FRANK HARDI | THE ABYSSINIAN CRISIS |
| GEORGE STEER | CAESAR IN ABYSSINIA |
| HENRI DE MONFREID | L'AVION NOIR |
| LEONARD MOSLEY | HAILE SELASSIA |
| L.SAVA | ETHIOPIA UNDER MUSSOLINI'S RULE |
| MARCEL GRIAULE | UNE VICTORE DE LA CIVILISATION |
| MARCEL JUNOD | LE TROISIEME COMBATTANT |
| MARIA GIACONIA LANDI | CROCE ROSSINA IN I.O.A. |
| PAOLO MONELLI | STORIA ILLUSTRATA |
| PAUL GENTIZON | LA CONQUETE DE L'ETHIOPIE |
| PIERRE ITCHAC | L'ILLUSTRATION |
| PIETRO BADOLIO | THE WAR IN ABYSSINIA |
| RAFFAELE CIASCA | STORIA COLONIALE DELL' ITALIA CONTEMPORANEA |
| RICHARD PANKHURST | ETHIOPIA OBSERVER |
| RODOLFO GRAZIANI | FRONTE SUD |
| SANDRO VOLTA | GRAZIANI A NEGHELLI |
| SEM BENELLI | IO IN AFRICA |
| THEODORE AUGENE KONOVALOFF | CON LE ARMATE DEL NEGUS |
| U. CAVALLERO | GLI AVVENIMENTI MILITARI NEL EMPERO DELL 12 GENNAIO |
| VITTORIO MUSSOLINI | VOLI SULLE AMBE |
| WILLIAM J. MAKIN | WAR OVER ETHIOPIA |
| በኢጣሊያ መንግሥት የወጡ | IL, ANNO DELL' IMPERO VOL I |
| | " " " " " II |
| | " " " " " III |



የዱቼ ሙሶሊኒ መጨረሻ
በስድስት ጥይቶች ከተገደሉ በኋላ
ከፍቅረኛ ሴት ወዳጃ ጋር
ተዘቅዝቀው ተሰቀሉ

ዋጋ አስር ብር ብቻ